# የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ፣ ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 16/2012

Guidelines Issued to Determine the Qualification Requirements for Registration and Work Permits for Animal Feed and Feed Raw Material Manufacturers, Importers, Wholesalers, Exporters, and Retailers (Directive No. 16/2012)


የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርናጥጥር ባለስልጣን
Veterinary Drug and Animal Feed
Administration and Control Authority

ነሀሴ 7፥ 2012

**ማውጫ** **ገጽ**


መግለጫ........................................................................................................................1

**ክፍል አንድ**
**አጠቃላይ**

1. አጭርርዕስ ....................................................................................................................2
2. ትርጓሜ.........................................................................................................................2
3. የመመሪያዉ ዓላማ .........................................................................................................6
4. የተፈጻሚነት ወሰን..........................................................................................................6

**ክፍል ሁለት**
**ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

5. የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ......................................................................................6
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት .................................................................6
7. የመኖ ንግድ ሥራ መስኮችና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ...................................................7
   1. የእንስሳት መኖ መፈብረክ 30330)…………………………………………………………..……….7
   2. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ መፈብረክ (30340……………………………………………..……..…….9
   3. የእንስሳትመኖ ጅምላ ንግድ (61266)…………………………………………………………..…..…11
   4. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ ንግድ (61258)……………………………………………………12
   5. የእንስሳት መኖ ችርቻሮ ንግድ (62260)……………………..……………...………………..……….13
   6. የእንስሳት መኖ አስመጪ (65266)……………………………...………………………..…...……15
   7. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ (65271)………………..………………………….....……..……16
   8. የእንስሳትመኖላኪ (66158)………………………….……………………………..…………….17
   9. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ (66172)……………..………………………………………..……….18
8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸዉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች………. ........................19
9. የንግድ አድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ .............................................................…..20
10. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለ መስጠት..............................................................…20
11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት......................................................................21
12. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ.................................................................21

**ክፍል ሦስት**
**ስለ መኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ**

13. የመኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች …………………………………….22
14. በመኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች.........................................23
15. የመኖ ንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ እና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት ...................................23

## ክፍል አራት

## ስለ መኖ ንግድ ድርጅት አመሠራረትና ተዛማጅ መስፈርቶች


16. የመኖ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ ሁኔታዎች ....24
17. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ ግንባታ አሠራር....25
18. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ዉስጥ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች....26
19. የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ወይም ማሸጊያ ዕቃዎች ሁኔታ ....26
20. በመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ላይ መኖር ስለሚገባዉ ገላጭ ጽሑፍ ....27


## ክፍል አምስት

## መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማስወጣት፣ ማከፋፈልና ማጓጓዝ


21. መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ስለማስገባት ....28
22. በመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች ....29
23. በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች ....30
24. መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ከሀገር ስለማስወጣት....31
25. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ ....31
26. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ስለማከፋፈል....32
27. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ስለማጓጓዝ....33


## ክፍል ስድስት

## አስተዳደራዊ እርምጃዎች


28. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት....33
29. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ....34
30. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ....34
31. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ስለመመለስ....35
32. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት ....35
33. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶችን ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ ....36
34. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ስለመያዝ....36
35. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ከገበያ ስለ መሰብሰብ (Feed Products Recall) ……….. 34
36. ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬዕ ቃ ምርቶችን ስለማስወገድ ....37
37. በባለስልጣኑ በሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት ....37


## ክፍል ሰባት

## መረጃ የመያዝ ግዴታ፣ የንግድ ማስታወቂያና የአገልግሎት ክፍያ


38. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መረጃ ስለ መያዝ....38
39. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ማስታወቂያ አሠራር ....38
40. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ....40
41. የአግልግሎት ክፍያ....41

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

42. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች ........................................................................41
43. መመሪያውን ስለ ማሻሻል ........................................................................................43
44. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ........................................................................................43
45. ዕዝሎች ..................................................................................................................44

## መግለጫ

በእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና የሚሰማሩ ድርጅቶች የሚያመርቱትን፣ከዉጭ ወደ ሀገር የሚያስገቡትን፣የሚያከፋፍሉትን፣ከሀገር ወደ ውጭ የሚልኩትን እና የሚቸረችሩትን መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የቀጥተኛ ተመጋቢዉን እንስሳ እንዲሁም የእንስሳት ምርት ተጠቃሚዉን ህብረተሰብ ጤና መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ሀገር የሚገባ መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠና አስፈላጊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ላይ በቂና ሕጋዊ ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ ለሚሰማራ ማንኛውም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ የንግድ አሠራር ሥርዓት ሆኖ በመገኘቱ፤

የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሥራዎችን ግልጽና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሠራር ለማካሄድ እንዲቻልና ተገልጋዮችም ይህንን አውቀው መደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት በማሟላት የአገልግሎት ጥያቄአቸውን በአግባቡ እንዲያቀርቡ ለማስቻል፤

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ28 ንዑስ አንቀጽ2 ለባለሥልጣኑ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ይህ የመኖ አምራች፣አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይ፣ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራፈቃድየብቃትማረጋጋጫመስጫ አሠራር መመሪያ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

ይህ መመሪያ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ ለተገልጋዮች ከተሰራጨዉ መመሪያ ቁጥር 03/2007 የሚለየዉ በንግድ ሚ/ር የመመሪያ ዝግጅት አሰራር መሠረት እንዲሁም የመኖ ችርቻሮ ንግድ ሥራን በማካተት የተዘጋጀ መሆኑ ነዉ፡፡

# ክፍል አንድ
# አጠቃላይ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይ፣ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ መስጫ አሠራር መመሪያ ቁጥር 16/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

በአዋጁ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. **"መኖ"** ማለት በመኖ አምራች ድርጅትበሀገር ዉስጥ የሚመረት፣ከዉጭ ወደ ሀገር የሚገባ፣በሀገር ዉስጥም ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ለንግድ የሚዘዋወር ወይም ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ለሽያጭ የሚወጣ የእንስሳት ምግብ ነው፡፡ ይህ ትርጉም ወደ ንግድ ቅብብሎሽ የሚገባዉን የሣር ድርቆሽ፣የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ተረፈ ምርትንና የጤፍ ጭድን የሚያካትት ሲሆን የንግድ መኖ መዘርዝር በሌላ ሰነድ የሚዘጋጅ ይሆናል፣
2. **"የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር"** ማለት ማንኛውም መደበኛ የእንስሳት አመጋገብን የንጥረ መኖ ፍላጎት ለማሟላት በይዘቱ የምግብነት ወይም መኖነት ያለዉ ወይም የሌለዉ ሆኖ በመኖ ዝግጅት ወቅት ለማጣፈጫ፣ለቀለም ማሳመሪያ ወይም ለማጣበቂያ (ቅርጽ ማስያዣ) ወዘተ በጥቂቱ የሚቀላቀል ንጥረ ነገር ሆኖ በእንስሳት ወይም በእንስሳት ምርት ተመጋቢ ክፍል ላይ ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት እንደማያስከትል የተረጋገጠ መጠነኛ ንጥረ ነገር ነዉ፤
3. **"የመኖ ግብዓት ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ"**ማለት ተፈላጊውን መሠረታዊ መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል መደባለቂያ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ሲሆን የሸንኮራ አገዳና ስኳር ተረፈ ምርት (ቁርጥራጭ፣ ባጋስ፣ ሞላሰስ) ፣ የምግብ ዘይትና ዱቄት ተረፈ ምርት (ፋጉሎ፣ፉሩሽካ፣ፉሩሽኬሎ፣ብጣሪ፣ እንቅጥቃጭ፣የካዛቫ ትርፍራፊ)፣የቢራና የአልኮሆል ፋብሪካ ተረፈ ምርት (የቢራ አተላ፣የአረቄአተላ፣የእርሾ አተላ፣የብቅል አሰርና እንቅጥቃጭ)፣የሳር ድርቆሽ (እርጥብ፣ ድርቆሽ፣የተቀረጣጠፈ፣ፔሌት ወዘተ)፣የዕርድ እንስሳት ተረፈ ምርት (ደም፣አጥንት፣ የስጋና ቆዳ ቅንጥብጣቢ፣አፋል፣ሽሆና፣የአሳ ተረፈ ምርት፣የዶሮ ኩስ ወዘተ)፣የመኖ

ተጨማሪ ማዕድናት (ኖራ፣ቦሌ፣ዳያአቶምስ፣ጨው ወዘተ)፣ ማይክሮ ባይሎጂካል የመኖ ማሻሻያ ግብዓቶች (ኢፌክቲቭ ማይክሮ ኦርጋኒዝም፣ ኢንዛይምስ ፣ ፕሮባዮቲክስ፣ፕሪባቲክስ ወዘተ) ይጨምራል፤

4. **"ዘረመሉ የተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው የመኖ ግብዓት"** ማለት በዘመኑ የዕፅዋትና እንስሳት ርቢ ምህንድስና፣በሰው ሠራሽ ዘዴ ከሌላ ሕያው የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር የተጨመረበት የዘረመሎች ይዘት፣ አቀማመጥና ባህርይ የተለወጠበት ሕያው የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤት ነዉ፤
5. **"ከአመንዣጊ እንስሳት ምርት የተገኘ የመኖ ግብዓት"** ማለት የሚያመሰኩ እንስሳት (የዳልጋ ከብት፣ጎሽ፣በግ፣ፍየል፣ግመል እና የመሳሰሉት) የተፈጨ ሥጋ፣ የደም፣ የአጥንት፣ የአንጎል፣ የአንጀት እና ሌሎች ምርት ዉጤት ነዉ፤
6. **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"**ማለት በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ ለሚሰማራ ማንኛዉም ድርጅት ወይም ተቋም አስፈላጊ ተቋማዊና የሰው ኃይል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ የንግድ ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የብቁነት ማረጋገጫ ወይም የሥራ ፈቃድ ነዉ፤
7. **"የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት ለእንስሳት መኖ ባለሙያ በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት የሚያስችል በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፤
8. **"የእንስሳት መኖ ባለሙያ"** ማለት ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም በእንስሳት ሳይንስ ወይም በእንስሳት መኖ እና ግጦሽ ልማትና አስተዳደር በዲፕሎማ ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የተመረቀ/ች እንዲሁም በመኖና በእንስሳት ሥነ-ምግብ ተጨማሪ ሥልጠና የወሰደ/ች ነዉ፤
9. **"የመኖ ፈቃድ ሰጪ አካል"** ማለት በባለሥልጣኑ የመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ወይም ዉክልና የተሰጠዉና ለተግባሩም አግባብነት ያለዉ አካል ነዉ፤
10. **"የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ"**ማለት የእንስሳት በመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ለንግድ ተግባር ማምረት፣ማዘጋጀት፣ከዉጭ ሀገር ማስገባት፣ወደ ዉጭ ሀገር መላክ፣ክልል ተሻጋሪ የጅምላ ማከፋፈል እና ችርቻሮ ንግድ ሥራ ነዉ፤
11. **"የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት"** ማለት ለንግድ ዓላማ መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን የሚገዛ፣የሚያመርት፣ከዉጭ የሚያስመጣ፣ወደ ዉጭ ሀገር የሚልክ፣በሀገር ዉስጥ በጅምላ በማከፋፈል ወይም በችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ

የተሰማራ ተቋም ነው፤

12. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ”**ማለት በሀገር ዉስጥ የተመረቱትን የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን በየብስ፣በባሕር ወይም በአየር ከኢትዮጵያ ወደ ዉጭ ሀገር የሚልክ ሰው ወይም ድርጅት ነዉ፤

13. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ”** ማለት ከሀገር ዉጭ የተመረቱ የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን በአየር፣በየብስ፣በባህር ወደ ሀገር በማስገባት ለመኖ ወይም ለመኖ ግብዓት ጅምላ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ተቋም ወይም ድርጅት ነዉ፤

14. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ አከፋፋይ”** ማለት ከሀገር ዉስጥ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ወይም አስመጪ በጅምላ በመግዛት ለመኖ ቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ተቋም ወይም ድርጅት ነዉ፤

15. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ችርቻሮ ንግድ”** ማለት መኖን ወይም የመኖ ግብዓትን ከአምራች፣ከአስመጪ ወይም ከጅምላ አከፋፋይ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

16. **“የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መሸጫ”** ማለት የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የሚሸጡበት መደብር ወይም ድርጅት ወይም ተቋም ነዉ፤

17. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ደረጃዎች”** ማለት በሀገሪቱ የደረጃዎች ኤጀንሲ የፀደቀና ኦፊሴላዊ ተቀባይነት ያገኘ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነት እንዲሁም ጤናማነቱ የተረጋገጠ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ነዉ፤

18. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማሸጊያ ወይም መያዣ”** ማለት የእንስሳት መኖ እንዲሁም የመኖ ግብዓቶችን ለመያዝ፣ለማጓጓዝና ለማከማቸት የሚጠቀሙበት መያዣ ዕቃ ነዉ፤

19. **“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ገላጭ ጽሑፍ”** ማለት በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ዕቃ ላይ የሚጻፍ ወይም የሚለጠፍ ወይም የሚታሰር ሆኖ ስለ መኖዉ ወይም መኖ ጥሬ ዕቃው ዓይነት፣የንጥረ ነገር ይዘት፣ለምን ዓይነት እንስሳት አመጋገብ እንደሚዉል፣የተመረተበት ቀን፣የአጠቃቀም አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፣ የአያያዝና ክምችት ሁኔታ ወዘተ የሚገልጽ ነዉ፤

20. **“መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን አስመስሎ ማቅረብ”** ማለት የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ይዘታቸዉ ከተቀመጠዉ ደረጃ በታች ወይም በይዘት ሳይሆን በዕይታ ብቻ ተመሳሳይ ወይም በሚያስመስሉ ባዕድ ነገሮች አስመስሎ ማቅረብ ነዉ፤

21. ***"መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን መከለስ"*** *ማለት ጥራትና ደህንነቱ አስተማማኝ ከሆነ ታዋቂ የመኖ ምርት ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ጋር ዝቅተኛና ተፈላጊውን ደረጃ በማያሟላ ወይም ባዕድ ነገር ጋር በመቀላቀልና በመከለስ ለገበያ ማቅረብ ነዉ፤*
22. **"የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ምስክር ወረቀት"** *አንድ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ጤናማ ስለመሆኑና መኖዉን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውን ለሚመገበዉ እንስሳ ወይም የእንስሳዉን ምርት ዉጤት (ሥጋ፣ወተት፣ዕንቁላል ወዘተ) በሚመገበዉ አካል ላይ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት እንደማያስከትል የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ነዉ፤*
23. ***"የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ዕገዳ"*** *ማለት* በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ወይም ተቋም ባለሥልጣኑ ያወጣቸውንና ተለይተው የተቀመጡ መስፈርቶችን ባለማክበሩ ምክንያት በዚህ መመሪያ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ ከመኖ ወይም ከመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ታግዶ እንዲቆይ የሚያደርግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤
24. ***"የመኖ ንግድ ሥራ ፈቃድ መሰረዝ"*** *ማለት በመኖ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ወይም ተቋም ባለስልጣኑ ያወጣቸዉንና ተለይተው የተቀመጡ መስፈርቶችን ባለማክበሩ ምክንያት በመኖ ንግድ ሥራ ላይ እንዳይሰማራ ለማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በመሰረዝ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤*
25. ***"የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራት ምርመራ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት"*** *ማለት እንደቅደም ተከተሉ በሀገር ውስጥ ለሚመረት፣ወደ ሀገር ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ይዘትን የሚገልጽና ደህንነትን የሚያረጋግጥ ሥልጣን በተሰጠዉ ተቆጣጣሪ የውጪ ሀገር አካል ወይም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤*
26. **"ባለሥልጣን"** *ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤*
27. **"አዋጅ"** *ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተደደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር* 728/2004 *ነው፤*
28. **"ሰው"***ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም ማለት ነው፤*
29. *ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡*

## 3. የመመሪያዉ ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣አስመጪ፣ላኪ፣ጅምላ አከፋፋይ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ተቋማዊ ብቃታቸዉን በማረጋገጥና አግባብነት ያለዉን የሥራ ፈቃድ በመስጠት የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነትን አስተማማኝነት በመጠበቅ ጤናማ የእንስሳት ምርት ዉጤት ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ለማስቻል ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነትወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ውስጥ ክልል እና ድንበር ተሻጋሪ የሆነ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ በማምረት፣ማስመጣት፣ጅምላ ማከፋፈል፣ወደ ዉጭ መላክ፣በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ ባለሙያነት የንግድ ሥራ ላይ በተሰማሩና በሚሰማሩ ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ መኖ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

## 5. መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ

1. ማንኛዉም ሰውከባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑን ከሚወክል አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ በእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤
2. ማንኛዉም ሰዉ በመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል አስፈላጊ የብቃት ማረጋጋጫ ለማግኘት በአንቀጽ 7 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ9 ድረስ የተመለከቱትን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰዉ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 መሠረት የንግድ ሚ/ር ወይም ሚንስቴሩን ከሚወክል አካል የንግድ ፈቃድ ሳያገኝ በእንስሳት መኖ እና በመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

## 6. የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀት ስለመስጠት

1. ማንኛውም ሰዉ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተጠቀሱትን መስፈርቶች በማሟላትና በዕዝል አንድ ሥር የተመለከተዉን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፤

2. የጠያቂዉ ድርጅት ወይም ተቋም ቅድመ ዝግጅትና ማመልከቻ የተሟላ ሲሆንናጠያቂዉ አካል ተገቢዉን ክፍያ ሲያሟላ ባለሥልጣኑ ከመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ Äይሬክቶሬት የተዉጣጣ ከሁለት አባላት ያላነሰ የአጣሪ ቡድን በመላክ ድርጅቱ እንዲታይለት ይደረጋል፤
3. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ሠራተኞች በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላታቸዉን በመፈተሽና በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠዉ ይደረጋል፤
4. ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ከተረጋገጠ እና ተገቢዉን የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ በኂላ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫዉን በሦስት የሥራ ቀናት ዉስጥ አጠናቆ ይሰጣል፤
5. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ7 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ ንኡስ አንቀጽ 9 የተዘረዘሩትን መሠረታዊ መስፈርቶች እንደ አግባብነታቸዉ በበቂ ሁኔታ ሳይሟሉ ለጠያቂዉ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም፣
6. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 5 በተጠቀሰው መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተከለከለ ድርጅት ፈቃዱ የማይሰጥበት ምክንያት በዝርዝር በጽሑፍ እንዲደርሰዉ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት ድርጅቱ እንዲያሟላ በጽሑፍ የተሰጠዉን መስፈርት አስተካክሎ ስለመገኘቱ ሲረጋገጥ ተገቢዉን ክፍያ በማስከፈል እንደገና ታይቶና ተረጋግጦ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የምስክር ወረቀቱ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 7. የመኖ ንግድ ሥራ መስኮችና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

### 1. **የእንስሳት መኖ መፈብረክ** (30330)

በዚህ የንግድ ሥራ መደብ የሚካተቱት የተመጣጠነ መኖ እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በማምረት ወይም በመፈብረክን ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ተቋማት ይሆናሉ፡፡

1. ማንኛዉም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች በሙሉ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፦

   ሀ. ከነባር የመኖ ማምረቻ ተቋማት በስተቀር ማንኛውምየመኖ ማምረቻ ድርጅትከሕዝብ መኖሪያ፣ ከጤና እና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ድርጅት

እንዲሁም ከእንስሳት ዕርባታ ጣቢያዎች ከ300 - 500 ሜትር ባላነሰ ርቀት ወይም ለኢንዱስተሪ ዞን በተከለለ አካባቢ መገኘት ይገበዋል፤

ለ. የመኖ ጥሬ ዕቃ መፈተሻና መረከቢያ ክፍል፣ የጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣ የማምረቻ ሰንሰለት፣የምርት ጥራት ፍተሻና ቁጥጥር ክፍል፣የምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ያለቀለት ምርት ማከማቻ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፣

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፤

መ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፤

ሠ. የሙቀት እና የዕርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር ያለበት ሲሆን የመሣሪያው ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል በየዓመቱ መፈተሸና መረጋገጥ ይኖርበታል፤

ረ. የመኖ ጥሬ ዕቃና ያለቀለት ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ሰ. በመኖ መሸጫ ክፍል ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ ዲጂታል ሚዛን መኖር አለበት፤

ሸ. አዲስ ለሚቋቋም የመኖ ማምረቻ ተቋም ወይም ድርጅት ከማምረቻዉ የሚወጣ ማንኛዉም ፍሳሽ፣ቆሻሻ ወይም ተረፈ-ምርት በአካባቢዉ የተፈጥሮ ሀብት እና በአካባቢው ሕዝብ ላይ የሚያደርሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለአለመኖሩ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት (Environmental Impact Assessment) ከመነሻዉ ተዘጋጅቶ ለባለሥልጠኑ ፈቃድ ሰጪ አካል ገቢ መደረግ አለበት፤

ቀ. ማንኛዉም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ እና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊነት መስፈርት የሚያሟሉ የመኖ ባላሙያዎችን በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ የገበዋል፤

በ. ማንኛዉም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ከፋብሪካዉ ዉጭ ተጨማሪ የመሸጫ ቅርንጫፍ ለመክፈት ሲፈልግ እንደማንኛዉም አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ተቋም የዚህን መመሪያ አሠራር በመከተል ለሚከፍተዉ ተጨማሪ መሸጫ ቅርንጫፍ የብቃት ማረጋገጫ መዉጣት አለበት፤ዕዉቅናም ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን መተላለፍ በሕግ

የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

2. የመኖ አምራች ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈርምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. አዲስ የሚቋቋም የመኖ ማምረቻ ተቋም ወይም ድርጅት ከሆነ ከማምረቻዉ የሚወጣ ማንኛዉም ፍሳሽ፣ቆሻሻ ወይም ተረፈ-ምርት በአካባቢዉ የተፈጥሮ ሀብት እና ነዋሪ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያደርስ ሁኔታ የማካሄድ ግዴታ፤

ለ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፤

ሐ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፤

መ. ለመኖ ማምረቻ ወይም መፈብረኪያ ተቋሙ ሕጋዊ የመሬት ፈቃድ፣ ካርታና የሳይት ፕላን ማቅረብ፣ወይም

ሠ. ለመኖ ማምረቻ ወይም መፈብረኪያ ተቋም የታሰበው መሬት የግል፣ የቡድን፣የማህበር ወይም በኪራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ፡፡

## 2. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ መፈብረክ (30340)

በዚህ የንግድ ሥራ መደብ ሥር የተሟላ ምጥን መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መደባለቂያዎችን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ማለትም እንደ ሸንኮራ አገዳና ስኳር ተረፈ ምርቶች፣የምግብ ዘይትና ዱቄት ተረፈ ምርቶች (ፋጉሎ፣ፉሩሽካ፣ ፉሩሽኬሎ፣ ብጣሪ፣እንቅጥቃጭ፣የካዛቫ ትርፍራፊ)፣የቢራና የአልኮሆል ፋብሪካ ተረፈ ምርቶች፣ የሳር ድርቆሽ፣የአልፋልፋ ምርት ዉጤቶች፣የመኖ ተጨማሪ ማዕድናት (ኖራ፣ ቦሌ፣ ዳይአቶምስ፣ጨው ወዘተ) መፈብረክን ያጠቃልላል፡፡

1. ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

ሀ. ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣የምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ ሊኖረው ይገባል፤

ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ

መሆን አለበት፣

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣

መ. የሙቀት እና የዕርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር ያለበት ሲሆን የመሣሪያው ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል በየዓመቱ መፈተሸና መረጋገጥ አለበት፣

ሠ. የመኖ ጥሬ ዕቃ በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ረ. በመኖ ጥሬ ዕቃ መሸጫ ክፍል ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ ጥሬ ዕቃ መመዘኛ ሚዛን መኖር አለበት፣

ሰ. ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛ ወይም በድሮው 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና በተጨማሪም መሰረታዊ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና የወሰደ የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርትና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል።

ሸ. ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ድርጅት የጥሬ ምርትን ጥራትና ደህንነት ለመጠበቅ በዚህ መመሪያ የተቀመጠዉን መስፈርት ለሚያሟሉ ሕጋዊ ብቃት ላላቸዉ አከፋፋይ ድርጅቶች ብቻ መሸጥ አለባቸዉ። ይህን መመሪያ መተላለፍ በሕግ የሚያስጠይቅ ይሆናል።

2. የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. ከላይ የተገለጸውን የትምህርት ዝግጅትና ስልጠና የወሰደ ሰራተኛ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

ሐ. ለመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ወይም መፈብረኪያ ተቋሙ ሕጋዊ የመሬት ፈቃድ፣ ካርታና የሳይት ፕላን ማቅረብ፣ወይም ለመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ወይም መፈብረኪያ ተቋም የታሰበው መሬት የግል፣ የቡድን፣ የማህበር

ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ፡፡

## 3. የእንስሳት መኖ ጅምላ ንግድ (61266)

የእንስሳትመኖጅምላንግድየተመጣጠነ መኖ በጅምላ የመሸጥን ሥራን ብቻይመለከታል፡፡

1. ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

ሀ. የመኖ ምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል እና ማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፣

ለ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣

ሐ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣

መ. የመኖ ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ሠ. በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ እንዲሁም የመኖ መመዘኛ ሚዛን በማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት

ረ. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የመኖ ምርቱን ሲያከፈፋፍል፤ አምራች ተቋም ካዘጋጀዉ ይዘት ዉጭ ማሸጊያዉን በመክፈት ክብደት የመጨመር ወይም የመቀነስ፤ ተጨማሪ ግብዓት የመክተት፣የመከለስ ወይም የመቀየጥ፣ መያዣና ገላጭ ጽሑፍ የመለወጥ ወይም የመቀየር ሥራ በፍጹም የተከለከለ ነዉ፡፡ በሕግም የሚያስጠይቅ ነዉ፡፡

ሰ. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሠራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፡፡

2. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ

ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

ሐ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን፣የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል፣የቡድን፣ የማህበር ወይም በኪራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ፡፡

## 4. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ ንግድ (61258)

በዚህ የንግድ ሥራ መደብ የሚያካቱት የተሟላ ምጥን መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መደባለቂያዎች ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ጅምላ ማከፋፈልን ለምሳሌ የሸንኮራ አገዳና ስኳር ተረፈ ምርቶች፣የምግብ ዘይትና የዱቄት ተረፈ ምርቶች፣ የቢራና የአልኮሆል ፋብሪካዎች ተረፈ ምርቶች፣ የሳር ድርቆሽ፣ የአልፋልፋ፣የዕርድ እንስሳት ተረፈ ምርቶች (ደም፣አጥንት፣የስጋና ቆዳ ቅንጥብጣቢ፣ ኦፋል፣ሸሆና፣የአሳ ተረፈ ምርት፣የዶሮ ኩስ ወዘተ)፣የመኖ ተጨማሪ ማዕድናት (ኖራ፣ ቦሌ፣ዳይአቶምስ፣ጨው ወዘተ)፣ ማይክሮ ባይሎጂካል የመኖ ማሻሻያ ግብዓቶች (ኢፌክቲቭ ማይክሮ ኦርጋኒዝም፣ኢንዛይምስ፣ፕሮባዮቲክስ ወይም ፕሪባዮቲክስ ወዘተ) ጅምላ ማከፋፈልን የሚያካት ይሆናል፡፡

1. ማንኛዉም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

ሀ. የመኖ ጥሬ ዕቃ መጫኛና ማራገፊያ መደላድል እና ማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፤

ለ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘኑ ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፤

ሐ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን  አለበት፤

መ. የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ምርት በመደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ሠ. የመኖ ጥሬ ዕቃዉ ምርት በፈሳሽ መልክ (የቢራና አረቄ ተረፈ ምርት፣ሞላሰስ እና የመሳሰሉት ፈሳሽ ይዘት ያላቸዉ) ከፋብሪካዎች በመረክብ የሚያከፋፍል ድርጅት ከምርቱ ልዩ ባህርይ አንጻር የማከማቻና የማጓጓዣ ሁኔታዉ ከደረቅ ምርቶች በተለየ መልኩ፣ በፈሳሽ ምርቶች መያዣና ማጓጓዣ ዘዴ በጥንቃቄ መጓጓዝ አለበት፤

ረ. ፈሳሽ የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት በፈሳሽ ምርቶች መያዣ በማጓጓዝ በመዳረሻዉ ቦታ ጥሬ ዕቃዉ የሚራገፈዉ ለፈሳሽ ምርት ማጠራቀሚያ በሚያመች ሁኔታ በተዘጋጀ የክምችት ዴፖ መሆን ይገበዋል፤

ሰ. በመኖ ጥሬ ዕቃ መጋዘን ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የዕርጥበት መለኪያ መሣሪያ እንዲሁም የመመዘኛ ሚዛን በመጋዘኑ መኖር አለበት፤

1. ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ ንግድ ድርጅት ቢያንስ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛ ወይም በድሮው 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና በተጨማሪም መሰረታዊ የመኖ ጥሬ ዕቃ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና የወሰደ የመኖ ጥሬ ዕቃ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሰራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፡፡

2. የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈርምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. ከላይ የተገለጸውን የትምህርት ዝግጅትና ስልጠና የወሰደ ሰራተኛ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. ፈሳሽ የመኖ ጥሬ ዕቃ ተቀባይ (ተጠቃሚ ወይም ቸርቻሪ) ለፈሳሽ ጥሬ ዕቃዉ ተስማሚ የፈሳሽ ጥሬ ዕቃ መከማቻ ዴፖ በማዘጋጀት መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተጠቃሚዎች ወይም ቸርቻሪዎች ብቻ የማቅረብ ኃላፊነት፤

ሐ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

መ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል፣ የቡድን ወይም የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 5. የእንስሳት መኖ ችርቻሮ ንግድ (62260)

የእንስሳትመኖችርቻሮንግድየተመጣጠነ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ምርት ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን እንዲሁም ወደ ንግድ ቅብብሎሽ የሚገባዉን የሣር ድርቆሽ፣የአልፋልፋ ምርት፣የዘይትና ዱቄት ተረፈ ምርት፣ የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ተረፈ ምርትንና የጤፍ ጭድ በችርቻሮ መሸጥን የሚያካትት ይሆናል፡፡

1. ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

   ሀ. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል እና የማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፣

   ለ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣

   ሐ. የመኖ እና/ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣

   መ. የመኖና መኖ ጥሬ ዕቃዎች ምርት በመደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ መደርደርና መከማቸት አለበት፤

   ሠ. ፈሳሽ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ምርት ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ የፕላስቲክ በርሜል ወይም ጄሪ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

   ረ. በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ እንዲሁም የመኖ መመዘኛ ሚዛን በማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት፣

   ሰ. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ቢያንስ የመጋዘን ሠራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ከማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፡፡

   ሸ. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ችርቻሮ ንግድ ድርጅት፤ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ሲቸረችር አምራቹ ተቋም ካዘጋጀዉ ይዘት ዉጭ ማሸጊያዉን በመክፈት ክብደት የመጨመር ወይም የመቀነስ፤ ተጨማሪ ግብዓት የመክተት፣የመከለስ ወይም የመቀየጥ፣ መያዣና ገላጭ ጽሑፍ የመለወጥ ወይም የመቀየር ሥራ በፍጹም የተከለከለ ነዉ፡፡ በሕግም የሚያስጠይቅ ነዉ፡፡

2. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈርምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

   ሀ. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና የወሰደ የሽያጭ ሰራተኛ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪውን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ ወይም በባለቤቱ ስራው የሚካሄድ ከሆነ ባለቤቱ በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና የወሰደ ስለመሆኑ ማስረጃ የማቅረብ፣

   ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ የመያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ፣

ሐ. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል ወይም የቡድን ወይም የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ፡፡

## 6. የእንስሳት መኖ አስመጪ (65266)

የእንስሳት መኖ አስመጪ የንግድ ሥራ መደብ የተመጣጠነ መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ከውጭ ወደ ሀገር የማስገባትን ሥራዎች የሚያካትት ይሆናል፡፡

1. ማንኛዉም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡
   ሀ. የመኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥር ነገር ምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ ያለቀለት ምርት ማከማቻ መጋዘን፣የምርት ጥራትና ደህንነት ፍተሻና ክትትል ክፍል ሊኖረዉ ይገባል፣
   ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣
   ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣
   መ. የመኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ምርት በመደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤
   ሠ. መኖ ወይም በመኖ ንጥረ ነገር ምርት መጋዘን ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር አለበት፣
   ረ. መኖ ወይም መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መሸጫ ክፍል ዉስጥ አግባብነትባለው ተቆጣጣሪ አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ ሚዛን  መኖርአለበት፣
   ሰ. የመኖ አስመጪ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሠራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፣
   ሸ. የመኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅት ስለሚያስመጣው መኖ በላኪው ሀገር የታወቀና የተመዘገበ አምራች ስለመሆኑ እንዲሁም የመልካም አመራረት ምስክር ወረቀት በሀገሪቱ ተቆጣጣሪ መ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከላኪው ድርጅት ጋር የተደረገ የንግድ ስምምነት ማስረጃ ወረቀት በቅድሚያ

ማግኘትና ከብቃት መረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2. የመኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅት የግዴታ ዉል የሚፈረምባቸዉ መስፈርቶች (Commitment paper)
   ሀ. ከላይ በተገለጸው የሙያ ዘርፍ ብቃት ያለውን ባለሙያ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪውን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣
   ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣
   ሐ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን፣ የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል የቡድን፣ ወይም የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 7. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ (65271)

ይህ የንግድ ሥራ መደብ ምጥን መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል መደባለቂያ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ከውጭ ወደሀገር የማስገባት ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

1. ማንኛዉም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-
   ሀ. የመኖ ጥሬ ዕቃ መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣የማከማቻ መጋዘን፣የጥሬ ዕቃ ጥራትና ደህንነት ፍተሻና ክትትል ክፍል ሊኖረዉ ይገባል፣
   ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣
   ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣
   መ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት በመደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤
   ሠ. በመኖ ጥሬ ዕቃ፣መጋዘን ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር አለበት፣
   ረ. በመኖ ጥሬ ዕቃ መሸጫ ክፍል ዉስጥ አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መመዘኛ ሚዛን መኖር አለበት፣

ሰ. የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሠራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፣

ሸ. የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ ድርጅት ስለሚያስመጣው የመኖ ጥሬ ዕቃ በላኪው ሀገር የታወቀና የተመዘገበ አምራች ስለመሆኑ እንዲሁም የመልካም አመራረት ምስክር ወረቀት በሀገሪቱ ተቆጣጣሪ መ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከላኪው ድርጅት ጋር የተደረገ የንግድ ስምምነት ማስረጃ ወረቀት በቅድሚያ ማግኘትና ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

2. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ ድርጅት የግዴታ ዉል የሚፈረምባቸዉ መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. ከላይ በተገለጸዉ የሙያ ዘርፍ ብቃት ያለውን ባለሙያ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪውን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

ሐ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል፣ የቡድን ወይም የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

## 8. የእንስሳት መኖ ላኪ (66158)

የእንስሳት መኖ ላኪ የንግድ ሥራ መደብ በተሟላ መልክ የተዘጋጀ የተመጣጠነ መኖ ወደ ውጭ ሀገር የመላክን ሥራ ይሆናል።

1. ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል:-

ሀ. የመኖ መፈተሻና መረከቢያ ክፍል፣የምርት ጥራት ፍተሻና ቁጥጥር ክፍል፣ የምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ያለቀለት ምርት ማከማቻ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፤

ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፤

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፤

መ. የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር ያለበት ሲሆን የመሣሪያው ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል በየዓመቱ መፈተሽና መረጋገጥ፤

ሠ. የመኖ ጥሬ ዕቃና ያለቀለት ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ረ. በመኖ መሸጫ ክፍል ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ ሚዛን መኖር አለበት፤

ሰ. ማንኛዉም የመኖ ላኪ ድርጅት ቢያንስ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ መስፈርት የሚያሟላ የመኖ ባለሙያ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገበዋል፤

ሸ. ማንኛዉም የመኖ ላኪ ድርጅት የምርቱ ተቀባይ አካል ወይም ሀገር የሚያቀርባቸውን የጥራትና የደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ምርት በኃላፊነት በማሟላት ማቅረብ ይገበዋል፤

2. የእንስሳት መኖ ላኪ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈርምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)፡-

ሀ. በተገለጸው የሙያ ዘርፍ ብቃት ያለው ባለሙያ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪውን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

ሐ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን፣የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል፣የቡድን፣ የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ፡፡

## 9. የእንስሳት መኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ (66172)

የንግድ ሥራ መደቡ ምጥን መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል መደባለቂያ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር እንዲሁም ወደ ንግድ ቅብብሎሽ የሚገባዉን የሣር ድርቆሽ፣የአልፋ አልፋ ጥሬ ምርት፣የዘይትና ዱቄት ተረፈ ምርት፣የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ተረፈ ምርትንና የጤፍ ጭድ ወደ ውጭ መላክን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

1. ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል:-

ሀ. የመኖ ጥሬ ዕቃ መፈተሻና መረከቢያ ክፍል፣የምርት ጥራት ፍተሻና ቁጥጥር ክፍል፣የምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል እና የማከማቻ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፣

ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን አለበት፣

መ. የሙቀት እና የዕርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር ያለበት ሲሆን የመሣሪያው ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል በየዓመቱ መፈተሽና መረጋገጥ አለበት፣

ሠ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት በመደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ፤ፈሳሽ ከሆነ በማይዝግና በማያፈስ በርሜል ወይም ፕላስቲክ ማከማቻ ውስጥ መከማቸት አለበት፤

ረ. በመኖ ጥሬ ዕቃ መሸጫ ክፍል ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ ሚዛን መኖር አለበት፣

ሰ.ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ድርጅት ቢያንስ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ መስፈርት የሚያሟላ የመኖ ባላሙያ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

ሸ. ማንኛዉም የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ድርጅት የምርቱ ተቀባይ አካል ወይም ሀገር የሚያቀርባቸውን የጥራትና የደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ምርት በኃላፊነት በማሟላት ማቅረብ ይገበዋል፤

2. የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)፡-

ሀ. በተገለጸው የሙያ ዘርፍ ብቃት ያለው ባለሙያ በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪውን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፣

ሐ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣ የመሸጫና ማሰራጫ ቦታ መሬት የግል፣ የቡድን፣ የማህበር ወይም በክራይ የተገኘ ስለመሆኑ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸዉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

1. ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ማዉጣት ሳያስፈልግ የእንስሳት መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ወደ ሀገር ለማስገባት ወይም ወደ ዉጭ ሀገር ለመላክ የሚቻልበት ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

ሀ. ለሳይንሳዊ ምርምር ጠቀሜታ የሚዉሉ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ናሙናዎች፣

ለ. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች የቤት እንስሳት ፍጆታ የሚዉል መኖ፣

ሐ. በድርቅ፣ጎርፍ፣የመሬት ነዉጥና በአጠቃላይ ለችግር ጊዜ ደራሽ ዕርዳታ የሚውል መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ፣

2. የእንስሳትን ሕይወት ለመታደግ ደራሽ መኖ የሚያቀርቡ ግለሰቦች፣ተቋማት ወይም ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያስፈልጋቸው፡-

ሀ. ከአካባቢው የግብርና ልማት ጽ/ቤት ወይም አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት ወይም የእንስሳት ሀብት ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት ወይም መስተዳድር አካል በአካባቢው ስለተከሰተው አደጋ የሚገልጽ ደብዳቤ በማቅረብ፣

ለ. ሕጋዊ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ካለው ድርጅት በመግዛት፣

ሐ. ስለተከሰተው ችግር እውነተኛነት ሲረጋገጥ ከባለሥልጣኑ ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ለመኖው ወይም ለመኖ ጥሬ ዕቃው የይለፍ ፈቃድ ደብዳቤ በማግኘት ወደ ተፈቀደው አካባቢ ማስተላለፍና ጥቅም ላይ ማዋል ይችላሉ፣

3. ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈጠረዉ አጋጣሚ ችግርና ሁኔታ በማሳበብ የሚከናወን ሕገ-ወጥ ተግባር በማስረጃ ሲረጋገጥ በሕግ አግባብ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

## 9. የንግድ አድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

1. ማንኛዉም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ የድርጅቱን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር እንዲሁም የባለቤትነት ለውጥ ማድረግ አይችልም፣
2. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሳያሳውቅ ሌሎች መጋቢ ወይምተጨማሪ መጋዘኖችን መክፈት አይችልም፡፡

## 10. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለ መስጠት

ቀደም ሲል የተሰጠዉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይምየጠፋበት ድርጅት ምትክ ሊያገኝ የሚችለዉ፡-

1. ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሽቱ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስና ምትክ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ ስለመጥፋቱ የሚገልፅ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ እና
3. ለምትክ አሰጣጡ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ብቻ ይሆናል፡፡

## 11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

ማንኛዉም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊታደስለት የሚችለዉ፡-

1. በወቅቱ ይዞት የሚገኘዉ የምስክር ወረቀት ታግዶ ወይም ተሰርዞ ካልሆነ፣ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ሥራዉን ካላቋረጠ፣
2. ባለሥልጣኑ ለዚህ ሥራ ዘርፍ ያወጣቸዉ መመዘኛዎች የተጠበቁ ስለ መሆናቸው በባለስልጣኑ የምዝገባና ፈቃድ ባለሙያዎች በዓመታዊ የአሠራር ክትትል ሲረጋገጥ፣
3. ድርጅቱ ለዕድሳት አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል፣ በየዓመቱ ለዕድሳት በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ (ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ባሉት ቀናት) ለዕድሳት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣
4. በዚህ አንቀጽንዑስ አንቀፅ3 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ የምስክር ወረቀቱ በተለያየ ምክንያት ካልታደሰ በመጀመሪያው የጥቅምት ወር 25 በመቶኛበህዳር ወር 50 በመቶ ታህሳስ ወር እና ተከታታይ የበጀት ዓመቱ ወራት 75 በመቶ ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት በመክፈል ማሳደስ ይቻላል፣
5. በዚህ አንቀጽንዑስ አንቀጽ3 እና 4 መሠረት ሳይታደስ የቀረ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ በንግድ ሥራው መቀጠል ከፈለገ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ አዲስ የብቃት ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት ማውጣት ይችላል፡፡

## 12. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ

ምስክር ወረቀት የዋናውን ቅጅ ሁልጊዜ በንግድ ቤቱ የሽያጭ ክፍል ዉስጥ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ ከንግድ ፈቃዱ ጎን ለጎን መስቀል ወይም ማስቀመጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ መኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ

### 13. የመኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች

1. ማንኛዉም የመኖ አምራች ድርጅት ቢያንስ የመኖ አመራረት ሂደት ኃላፊ እና የምርት ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን ቀጥሮ ማሠራት አለበት፤
2. የመኖ ባለሙያዎችም በእንስሳት ሳይንስ ወይም በእንስሳት ሳይንስና ግጦሽ መሬት አስተዳደር በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ ሆነዉ በመኖ ዝግጅት፣ ቅንብርና ማኔጅመንት የተለየ ሥልጠና በመውሰድ ልዩ ሰርቲፊኬት ወይም ዲፕሎማ ሊኖራቸዉ ይገባል፤
3. ማንኛዉም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ለክምችትና ጅምላ ማከፋፈል ሥራ የቴክኒካዊ አሠራርን በኃላፊነት የሚመራ የመጋዘንና የሽያጭ ሠራተኛ የመኖ ባለሙያ ቀጥሮ ማሠራት አለበት፡፡ የሠራተኞች የትምህርት ዝግጅትና የብቃት መስፈርት የሚከተለው ይሆናል፡-
   - ሀ. በድሮው የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከ12ኛ ክፍል በኂላ በኮሌጅ ደረጃ በሚሰጥ ሥልጠና በእንስሳት ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀና በመኖ አያያዝና አጠቃቀምየ ልዩ ሥልጠና ሰርቲፊኬት ያለው፤
   - ለ. በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ATVET) በደረጃ ሁለት (II) የተመረቀና በእንስሳት መኖ ዓይነትና ባህሪያት እንዲሁም ክምችት፣ አያያዝ፣አጠባበቅና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ሥልጠና መዉሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ምስክር ወረቀት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

## 14. በመኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች

1. በ መኖ የንግድ ሥራ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሙያ በእንስሳት ሳይንስ ወይም በእንስሳት ሳይንስ እና ግጦሽ መሬት አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪና የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ ወይም ሁለተኛ ዲግሪና የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ወይም የሦስተኛ ዲግሪና ዜሮ ዓመት የሥራ ልምድ ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ፣
2. በ መኖ የንግድ ሥራ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የማስተማር፣ የጥናት፣ የምርምርና የማማከር ሥራ ቀደም ሲል በዚሁ በተጠቀሰው ዘርፍ ስለ መሥራታቸው በቂ ማስረጃ ማቅረብ፣
3. በ መኖ ንግድ ሥራ ዘርፍ የማስተማር፣ የጥናት፣ የምርምርና የማማከር ዘርፍ ሙያ ሳይኖራቸው የማማከር አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለመክፈትና በሥራው ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ ሀ እስከ ንኡስ አንቀጽ ለ ድረስ የተጠቀሱትን የሙያ ዘርፍና የሥራ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ መረጃ በዝርዝር ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. በ መኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ የግዴታ ውል የሚፈርምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)፡-

   ሀ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

   ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፡፡

## 15. የመኖ ንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ እና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. የ መኖ ንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ ድርጅቱ በሚያመርተው፣ በሚያስመጣውና በሚያከፋፍላቸው የእንስሳት መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገሮች ወይም ግብዓቶች ላይ ለሚከሰቱ የጥራትና ደህንነት ችግር ሁኔታ መከታተልና ጉዳት ከመከሰቱ በፊት ችግሩን ለባለ ድርጅቱ በአፋጣኝ ማሳወቅ አለበት፤

2. በ ዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ለተከሰተው ችግር በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ የቴክኒክ ሠራተኛው ወይም ባለሙያው ለባለስልጣን መ/ቤቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

3. ከ መኖ ደህንነትና ጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ ለሚከሰት ማንኛውም ችግር ከድርጅቱ በተጨማሪ የቴክኒክ ሠራተኛው ወይም ባለሙያው ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ መኖ ንግድ ድርጅት አመሠራረትና ተዛማጅ መስፈርቶች

### 16. የመኖ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ ሁኔታዎች

ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የሚቋቋምበት አካባቢ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡ እነዚህም፡-

1. ለመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ አመቺ የመሠረተ ልማት አዉታሮች (ዉኃ፣ መብራት፣ የማመላለሻ መንገድ፣ ስልክ ወ.ዘ.ተ) ተሟልተዉ የተሠሩበት አካባቢ መሆን አለበት፣
2. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘን ከነዳጅ ማደያ፣ቄራ፣የእንስሳት ማራቢያ ጣቢያ፣ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ (ሆቴል፣የጤና ተቋም፣ትምህርት ቤት ወ.ዘ.ተ) ተቋማት ቢያንስ ከ300 እስከ 500 ሜትር ርቆ ወይም ለኢንዱስትሪ ዞን በተከለለ አካባቢ ሆኖ መኖን ሊበክሉ ከሚችሉ ከኬሚካል ማምረቻ ወይም መጋዘን፣ከሲሚንቶ ወይም ብናኝና ሽታ ካላቸዉ ፋብሪካዎች ርቆ እንዲሁም ከተጠቀሱ ተቋማት በስተምሥራቅ አቅጣጫ መገኘት አለበት፣
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንኡስ አንቀጽ 9 እና ከአንቀጽ 8 እስከ 14 የተመለከቱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ በተጨማሪም የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘንና አካባቢዉ መኖን ሊበክሉ ከሚችሉ መርዛማ ይዘት ካላቸዉ ነገሮች እንዲሁም በመኖዉ ተመጋቢ እንስሳት ብሎም በእንስሳት ምርት ዉጤት ተመጋቢ

ህብረተሰብ ጤና እና ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ወይም የጎንዮሽ ጉዳት ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነ አካባቢ መሆን ይገባዋል፡፡

## 17. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ ግንባታ አሠራር

1. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የሚደራጅበት ቦታ ከሽታና ብናኝ የፀዳ አካባቢ ሆኖ ከማምረቻዉ የሚወጣ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ሊኖረዉ ይገባል፤
2. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የጥሬ ዕቃ መፈተሻ፣ ማራገፊያ እና መጫኛ መደላድል፣ መረከቢያና ማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፤
3. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የማምረቻ ሂደት (ማበጠሪያ፣መፍጫ፣መደባለቂያ፣ ማድረቂያ፣ መመዘኛ፣ማሸጊያ፣የመግለጫ ጽሁፍ ወ.ዘ.ተ) ሥራዎች የሚከናወኑበት የአሠራር መስመሮች በግልጽ መቀመጥና መታየት አለባቸዉ፤
4. የግንባታዉ አሠራር ለዚህ ተግባር ለሚዉሉ ሕንፃዎች በሚወጣ ደረጃና መስፈርት መሠረት የማምረቻ ወይም የማከማቻ ተቋም ተለይቶ አግባብ ባለዉ የምህንድስና ተቋም የተረጋገጠ መሆን ይገባዋል፤
5. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን በምርቱ ጥራትና ጤናማነት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤
6. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ስፋት በምርቱ ብዛትና የክምችት ቆይታ ጊዜ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የሚወሰን ሆኖ የማከማቻ መጋዘንና የመሸጫ ክፍል ግን ተለያይተዉ መሠራት ይገባቸዋል፤
7. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ከፍሳሽ፣እርጥበትና ሌሎች የመኖን ምርት ለብልሽት ሊያጋልጡ ከሚችሉ ነገሮች ለመጠበቅ በምርት መደርደሪያ ዕቃ ወይም ከጣዉላ ወይም ከፕላስቲክ የተሠራ መደርደሪያ ፓሌት ላይ መደርደርና መጠበቅ ይኖርበታል፤
8. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ወለል ዉኃ የማያቀርና በሸካራ ሊሾ የተሰራ ሆኖ ግድግዳዉ ከሸክላ ወይም ብሎኬት ወይም ቆርቆሮ እና ከመሳሰሉት የተሠራና በሩ እና መስኮቱ እንዲሁም የአየር መዘዋወሪያ ቬንቶች በወንፊት ሽቦ የተሸፈኑና አይጥ፣ወፍ እና ሌሎች እህል በል የሆኑ ነፍሳትን የማያስገባ መሆን አለበት፤
9. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ መዋል ከማይችሉ መኖ እና የመኖ ግብዓቶች የፀዳ መሆን ይገባዋል፡፡ ጥቅም ላይ መዋል የማይገባቸዉ መኖ እና የመኖ ግብዓቶች በአግባቡ ማስወገድ እስከሚቻልበት ወቅት ድረስ የተለየ የማከማቻ ክፍል ወይም መጋዘን ዉስጥ በተለየ ሁኔታ በጽሑፍ ተገልጾ መጠበቅ ይገባል፤የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘን የድርጅቱ ሠራተኞች መገልገያ መጸዳጃ፣መታጠቢያና የልብስ መቀየሪያ ክፍሎች እንዲሁም የእሳት አደጋ መከላከያ አነስተኛ መሣሪያ ሊኖሩት ይገባል፡፡

## 18. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ዉስጥ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች

1. መኖ እና የመኖ ግብዓቶች በመጋዘን ዉስጥ ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ በሚከማቹበት ወቅት ከማንኛዉም ብልሽት ለመጠበቅ ከወለል በላይ ቢያንስ 10 ሳ.ሜ ከፍ ብለው በሚሠሩ መደርደሪያ ፓሌቶች ላይ፣ከግድግዳ 50 ሳ.ሜ ርቀው፣በድርድሮች መሀል በቂ መረማመጃ እንዲኖር ተደርጎ እና ከጣራ በታች 50 ሳ.ሜ ዝቅ ብለው ከነመያዣቻዉ መከማቸት አለባቸው፤
2. በመጋዘኑ ዉስጥ የሙቀትና የዕርጥበት መለኪያዎች (ቴርሞ እና ሀይግሮ ሜትር) በቅደም ተከተላቸዉ መኖርና በአግባቡ ማስቀመጥ ይገባል፡፡ የዉስጥ ሙቀት የመኖ ምርት ለብልሽት የሚዳርግበት ደረጃ የሚደርስ ከሆነ እንደየአካባቢዉ ሁኔታ የዉስጥ ሙቀትን ማቀዝቀዝ የሚችል ከመጋዘኑ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ ቬንትሌተር ማስገባት ይገባል፤
3. የመኖ እና የመኖ ግብዓቶች ሽያጭ ትክክለኛ ክብደት በሚያሳይ ሚዛን መሆን አለበት፣
4. የሚዛኑ ትክክለኛነትም በሚመለከተው አካል በየዓመቱ በመፈተሽና በማረጋገጥ ሲሆን የፍተሻዉ ማረጋጋጫ ወረቀት በሚዛኑ አጠገብ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 19. የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ወይም ማሸጊያ ዕቃዎች ሁኔታ

1. የመኖ እና መኖ ግብዓት መያዣ ዕቃዎች፣ማሸጊያዎች፣መደርደሪያዎች ሁሉ ከዝገት እንዲሁም መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች የፀዱ መሆን አለባቸው፤
2. የመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ዕቃዎች፣ማሸጊያዎች፣ለዚህ ተግባር እንዲዉሉ በመኖ ደረጃዎች ዝግጅት በሚወሰነዉ መሠረት በዝርዝር የሚገለጽ ቢሆንም ማንኛዉም መያዣ ወይም ማሸጊያ ከቃጫ ወይም ከፕላስቲክ ክር የተሠራና ምርቱን በማያፈስ ሁኔታ መሰፋት አለበት፤
3. ማንኛዉም የመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ከፕላስቲክ ወይም ከዝገት ነፃ ከሆነ ዕቃ የተሠራ መሆን አለበት፡፡ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ከፀረ-ተባይና የአፈር ማዳበሪያ፣የቁሳቁስ ማፅጃ ኬሚካሎች፣ናፍታ፣ከነዳጅና ቅባት ነገሮች እንዲሁም ከበርበሬ ወይም ከተለያዩ ቅመማቅመም ጋር የተነካካ መሆን የለበትም፤
4. ማንኛዉም የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ለመኖ መያዣነት ብቻ ተለይቶ በጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡ በተደጋጋሚ ለመያዣ አገልግሎት የሚዉለዉም ለመኖ ብቻ ሆኖ ለሌሎች ዕቃዎች ወይም የንግድ እህሎች መያዣ አገልግሎት መዋል የለበትም፤
5. ማንኛዉም ፈሳሽ የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ከአቧራና ብናኝ ነገር ለመከላከል እንዲቻል

በፕላስቲክ ወይም ከዝገት ነፃ በሆነ መያዣ ዉስጥ መያዝ አለበት፡፡ መያዣዉም ከፀረ-ተባይና የቁሳቁስ ማፅጃ ኬሚካሎች፣ናፍታ፣ከነዳጅና ቅባት ነገሮች ጋር የተነካካ መሆን የለበትም፡፡

## 20. በመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ላይ መኖር ስለሚገባዉ ገላጭ ጽሑፍ

1. ማንኛዉም ለንግድ አገልግሎት የሚዉል የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በማሸጊያዉ ላይ ገላጭ ጽሑፍ ካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊቀርብ ወይም ሊዘዋወርና ለሽያጭ ሊሰራጭ አይችልም፣
2. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ገላጭ ጽሑፍ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ (ወደ ዉጪ የሚላክ መኖ በተቀባይ ሀገር ጥያቄ መሠረት ይሆናል) በመኖ መያዣዉ ላይ ግልጽ፣ጉልህና በማይለቅ ቀለም መጻፍ አለበት፡፡ የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ገላጭ ጽሑፍ ዝርዝር ይዘት የሚከተሉትን የሚያካትት መሆን አለበት፡-

ሀ. የመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ የሚገልጽ፤

ለ. የመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ወይም የብራንድ ስም የሚገልጽ፤

ሐ. መኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው የተመረተበት ቀንና ዓመተ ምህረት፣

መ. የመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ምርት መለያ ቁጥር (Batch number)፣

ሠ. መኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው መጠቀሚያ የሚያበቃበት ጊዜ (ወርና ዓ.ም)፣

ረ. መኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ንጥረ ነገሮች ዝርዝር ይዘት ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸዉ፣

ሰ. የመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ምርት የተጣራ ክብደት (በግራም፣ በኪ.ግ)፣

ሸ.መኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ለየትኛዉ የእንስሳት ዓይነት፣የዕድሜ ክልል፣ የምርት ዓይነትና ደረጃ እንደተዘጋጀ የሚገልጽ (የወተት ዳልጋ ከብት፣የዳልጋ ከብት ማድለቢያ፣የበግ ወይም የፍየል ማድለቢያ፣ለዕንቁላል ጣይ ዶሮ፣ለሥጋ ዶሮ፣ ለጫጩት፣ለጥጃ ወዘተ) በማካተት የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ በግልጽ መስፈር አለበት፤

ቀ. መኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ስለሚጓጓዝበትና ስለሚከማችበት ሁኔታና መደረግ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ ወይም ማስገንዘቢያ ወይም ማስጠንቀቂያ በገላጭ ጽሑፍ ላይ በማካተት በግልጽ በሚነበብና በማይለቅ ቀለም መስፈር ይገባዋል፡፡

# ክፍል አምስት
# መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ማስገባት፣ ማስወጣት፣ ማከፋፈልና ማጓጓዝ

## 21. መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ስለማስገባት

1. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ንግድ ድርጅት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፤
2. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በዚህ የመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሠራር መመሪያ መሠረት መመዝገብ አለበት፤
3. ማ

   ንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በላኪው ሀገር የተመዘገበና ከሚመለከተው የላኪው ሀገር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የመልካም አመራረት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለው ድርጅት የተመረተ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፤
4. ማ

   ንኛውም መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር የሚገባው ሕጋዊ የመኖ ማስገቢያ ፈቃድ በተሰጠዉ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጪ ድርጅት ብቻ ነዉ፤
5. በ

   ዚህአንቀጽበንዑስ አንቀጽ4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአስቸኳይ አደጋና ለእንስሳት ሕይወት አድን ተግባር ሲባል የዕርዳታ ሰጪ ድርጅት ከውጪ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ለመስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ በአንቀጽ10 ንኡስአንቀጽ2 መሠረት የጥራትና ደህንነት መስፈርቶችን በማረጋገጥ የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጠዋል፤
6. ማ

   ንኛውም ወደ ሀገር ለሚገባ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የማስገቢያ ፈቃድ የሚሰጠዉ ሀገሪቱ ባወጣችዉ ወይም የተቀበለቻቸዉን ዓለም አቀፍ የመኖ ጥራት ደረጃዎችን አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነዉ፤
7. ማ

   ንኛውም ወደ ሀገር የሚገባ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የሚከተሉትን የማረጋገጫ ሰነዶች የያዘ መሆን አለበት፡፡

   ሀ. የመኖውን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውን ጤናማነትና ደህንነት የሚገልጽ የጤና ምስክር ወረቀት (Sanitary or phytosanitary Certificate) ፤

   ለ. የመኖዉን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውን ንጥረ ነገሮች ዝርዝር ይዘት ከትልቅ ወደ

ትንሽ በቅደም ተከተላቸዉ፣

ሐ. የምርት ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት (Certificate of Batch Analysis)፤

መ.የመልካም አመራረት ተሞክሮ ሰርተፍኬት (Good Manufucturing Practices (GMP) Certificate) ፤

ሠ. ዘረመሉ ከተለወጠ ግብዓት ነፃ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (Genetically Modified Organism (GMO) Free Certificate)፤

ረ. ከአመንዣጊ እንስሳት ፕሮቲን ምርት ዉጤት ነፃ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ሰርቲፊኬት (Ruminant Origin Protein Free Certificate) ፡፡

8. በዚህ አንቀጽ፣ንዑስ አንቀጽ፣ ረ የተመለከተው ከአመንዣጊ እንስሳት ፕሮቲን ምርት ነፃ የመሆን መስፈርት ለቤት እንስሳት ምግብ (Pet Animals Food) የሚውለውን ምርት አያካትትም፤

9. ከልዉጥ ሕያዉ ወይም ዘረመሉ ከተለወጠ ግብዓት የተቀመመ ወይም የተቀነባበረ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ (Processed from GMO Products) ወደ ሀገር ለመስገባት ፍላጎት ያለው ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 655/2001 አንቀጽ5 እና 20 መሠረት በደንና አካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር ፈቃድና ቁጥጥር አሠራር ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

10. ማንኛውም ወደ ሀገር የሚገባ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ገላጭ ጽሑፍ በአንቀጽ19 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

## 22. በመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች

ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬት አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠና ከ3 ወር በላይ ያልቆየ ኦርጅናል ሰነድ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ መሆን አለበት፡-

1. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬት ሰጪ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
2. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬቱ መለያ ቁጥር፤
3. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ምርመራ የተደረገበት ቀንና ዓመተ ምህረት፤
4. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፍኬት ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስም፣ አድራሻና ማህተም፣
5. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪውና የተቀባይ ድርጅቱ ስምና ሙሉ አድራሻ፤
6. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ዓይነት ዝርዝርና መጠን በኪ.ግ ወይም በቶን፤
7. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪዉ ኢንቮይስ (ደረሰኝ) ቁጥር፤
8. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጤና ሰርተፊኬቱን ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስምና

ኃላፊነት፣አድራሻና የጤና መርማሪ ድርጅቱ ማህተም በግልጽ መስፈር አለበት፡፡

## 23. በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች

ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ዋናው ቅጂ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎችን ማካተት አለበት፡-

1. ምርመራውን ያካሄደው ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፣
2. የመኖው ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው አምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
3. የመኖው ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው መጠሪያ ስም፣የተመረተበት ቀንና ዓ.ም እንዲሁም የመጠቀሚያው ጊዜ ወርና ዓ.ም፣
4. የምርት ባች መለያ ቁጥር (Batch number)፤
5. የተካሄደው ዝርዝር የምርመራ ዓይነት፣የተገኘው ውጤትና የተጠቀሙበት የምርመራ ዘዴ፣
6. ምርመራ የተደረገበት ቀንና ዓ.ም፤
7. የምርመራዉን ውጤት ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስም፣አድራሻና የመርማሪ ድርጅቱ ማህተም በግልጽ መስፈር አለበት፡፡

## 24. መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ከሀገር ስለማስወጣት

1. ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የላኪነት wYM ማዉጫ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወደ ውጭ ሀገር መላክ አይችልም፤
2. ማንኛዉም ወደ ወጭ ሀገር የሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በባለሥልጣኑ የተመዘገበና አምራች ድርጅቱም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፤
3. ማንኛዉም ወደ ወጭ ሀገር የሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የጤና ሰርተፊኬት ወይም የሳኒተሪ ወይም የፋይቶ ሳኒተሪ ሰርተፊኬት ማግኘት ይኖርበታል፡፡ çñM አንድ የጤና ሰርተፊኬት የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ጭነት (Consignment) ብቻ ነው፤
4. ማንኛውም ወደ ዉጭ ሀገር የሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ፈቃድ የሚሰጠዉ ሀገሪቱ ባወጣችዉ ወይም በተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የመኖ ጥራት ደረጃዎች እና ተቀባይ ሀገር የሚያቀርበዉን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

## 25. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ

1. ማ ንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የሚያከማቸውን መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ እንደምርቶቹ ልዩ ባህሪይና ዓይነት ማከማቸት አለበት፣
2. የ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት መኖውን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ፀረ-ተባይና ሌሎች ኬሚካሎች ጋር አብሮ ማከማቸት የለበትም፣
3. የ ተበላሹ፣የተከለሱ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች እስኪ.ወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው ከሌሎች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልፅ ፅሁፍ በመለጠፍ ለብቻ መቀመጥ (መደርደር) አለባቸው፣
4. የ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ሊያበቃ አጭር ጊዜ የቀራቸውን መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን በቅድሚያ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማድረግ አለበት፣

5. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ንፁህ፣ደረቅ፣ከመደበኛ የክፍል ሙቀት ብዙ ያልበለጠ፣ከተባይና እህል በል ተባይ ወይም እንስሳት ነፃ መሆን አለበት፤

6. በየመጋዘኑ እና በተለያዩ የመጋዘን ክፍሎች የምርት ዓይነት፣ምርቱ ያለበት ሁኔታ (status) እና ሌሎች ስለ መኖ ወይም መኖ ጥሬ ዕቃ ዝርዝር መግለጫ መረጃዎች በየጊዜው በማደስ መለጠፍ አለባቸው፡፡

7. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን እንደምርቱ ዓይነትና ባህሪይ በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ16 እስከ አንቀፅ17 በተዘረዘሩት መሠረት የማከማቻ መጋዘን መስፈርቶችን ያሟላ መሆን ይገባዋል፡፡

## 26. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ስለማከፋፈል

1. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት መኖን መግዛት የሚችለው በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠውና ከተመዘገበ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አስመጭ ወይም ከአገር ውስጥ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ድርጅት ብቻ መሆን አለበት፣
2. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ንግድ ድርጅት በክምችትና በአጓጓዝ ሂደት ወይም በማንኛውም ምክንያት ብልሽት ያልደረሰበትና ተገቢውን የጥራትና የደህንነት ደረጃ የጠበቀ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ብቻ ማከፋፈል አለበት፣
3. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ድርጅት ለገዢው የውስጥ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ለንግድ የሚውል መኖን ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ሕጋዊ ፈቃድ ለሌለው ግለሰብ ወይም ድርጅት መሸጥ አይችልም፣
4. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አከፋፋይ ድርጅት ለሚያከፋፍላቸው መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የግዥና የሽያጭ ደረሰኝ ሊኖረው ይገባል፣
5. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አከፋፋይ ድርጅት የሚያከፋፍለው መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በአንቀፅ 20 ላይ ስለ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላና መጀመሪያ ከነበረው መልክና ሁኔታ ምንም ዓይነት ለውጥ ወይም መቀነስ ወይም መከለስ ያልተደረገበትና ብልሽት ያልደረሰበት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መሆን ይገበዋል፡፡

## 27. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃን ስለማጓጓዝ

1. ማንኛውንም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በአቧራ፣ኬሚካል፣ነዳጅና ቅባት፣በባዕድ ነገሮች ወ.ዘ.ተ ለብክለት በሚያጋልጥ ሁኔታ ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፣
2. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማጓጓዣ መሣሪያ ንፁህ፣ደረቅና ምርቱን ከማናቸውም ብክለት የሚከላከል ስለመሆኑ በውስጥ የጥራትና ደህንነት ባለሙያ መረጋገጥ አለበት፣
3. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች የሚጫኑትና የሚራገፉት ማንኛውም እርጥበት ምርቱን በማይነካበት ሁኔታ መሆን አለበት፣
4. ከመኖ ወይም ከመኖ ጥሬ ዕቃዎች ጋር የሚቃረን ባህሪ ያለው ወይም ምርቱን ሊበክል ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ዕቃ በተጫነበት ማጓጓዣ መጫንና ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፣
5. ተገዝቶ ወይም ለሽያጭ የሚጓጓዘው መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወደ ሚፈለግበት የማከማቻ መጋዘን በአጭር ቀንና ጊዜ ውስጥ በጥንቃቄ እንዲደርስ መደረግ አለበት፤
6. ፈሳሽ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓት ከሚመረትበት ወደሚከማችበት ወይም ወደሚከፋፈልበት ቦታ ሲጓጓዝ፤ ለፈሻሽ ምርቶች ማጓጓዣ በሚስማማዉ ዓይነት ከብልሽት ነፃ በመሆነ መያዣ (ቦቴ፣ፕላስቲክ ሮቶ --- ወዘተ) መጓጓዝ አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት
# አስተዳደራዊ እርምጃዎች

## 28. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት

1. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ይህንን መመሪያና ሌሎች ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነና ጥፋቱ በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን የሚያሳግድ፣የሚያሰርዝ ወይም ሌሎች ከባድ አስተዳዳራዊ እርምጃዎችን የሚያስወስድ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደ አግባቡ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፣
2. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ድርጅቱ አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ በዚህ መመሪያ

ከአንቀጽ 29እና አንቀጽ30 በዝርዝር በተመለከተው መሠረት ተገቢውን እርምጃ ሊወsድበት ይችላል፡፡

## 29. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ

ማንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ባለስልጣኑ ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊያግድበት ይችላል፡፡

1. ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ከሌለው ድርጅት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ከገዛ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተቀበለ ወይም የሥራና የንግድ ፈቃድ ለሌው ድርጅት ሸጦ ከተገኘ፣
2. ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅቱን የቦታና አድራሻ ለዉጥ ካደረገ፣
3. በኢትዮጵያ የወጣውን ወይም ሀገሪቷ የተቀበለችውን የጥራት ደረጃዎች የማያሟላ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በመኖ ንግድ ገበያ ላይ አውሎ ከተገኘ፣
4. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ለማጓጓዝ የወጡትን መስፍርቶች በማይጠብቅ ሁኔታ ካጓጓዘ፣ካከማቸ ወይም ሲሸጥ ከተገኘ፣
5. ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የቁጥጥር ሥራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት ከሆነ ወይም ችግር የፈጠረ እንደሆነ፣
6. በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ7 ንዑስ አንቀጽ1 እስከ ንዑስ አንቀጽ3 ከተጠቀሱት መስፈርቶች መካከል ጉድለትና ጥፋት ሲገኝበት፣
7. በባለሥልጣኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድርጅቱ የማያስተካክል ከሆነ ወይም የኅብረተሰቡንና የአካባቢውን ጤና በማይጎዳ ሁኔታ እንዲመረት መመሪያው ባስቀመጠው መሰረት የምርት ሂደቱን ካልፈፀመ፣

## 30. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

ማንኛዉም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከመመሪያው አሠራር ውጭ በሆነ መንገድ የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ወረቀቱን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ፤
3. ማንኛውንምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ከሚገባው ይዘት በላይ ክብደት ለመጨመር

ወይም በቀለም ማስዋቢያ ወይም ሌላ ባዕድ ነገር ጨምሮና ከልሶ ወይም አስመስሎ በማቅረብ ሥራ ላይ ከተገኘ፤

4. ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካወጣበት የምርት ዓይነት ውጪ ሲያመርት፣ ሲያስመጣ፣ወደ ውጭ ሲልክ ወይም ሲያከፋፍል ከተገኘ፤
5. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ማስመዝገብ ሲገባው ያላስመዘገበ፣ የተበላሸ፣ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈበትን፣ገበያ ላይ እንዳይውል የታገደ፣ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሑፍ የሌለው ወይም አሳሳች ገላጭ ጽሑፍ ያለውን የያዘ፣የሸጠ ወይም ያከፋፈለ፣የከለሰ፣ አስመስሎ ያቀረበ፣በሕገወጥ መንገድ ንግድ ውስጥ የገባ፤
6. ከአምራቹ ድርጅት የውል ስምምነት ሳይኖረው በቅድሚያ የታሸገ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ እንደገና ከፋፍሎ በማሸግ ወይም ሌላ ገላጭ ጽሑፍ በማድረግ ከሸጠ፤
7. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ13 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በወቅቱ ካላሳደሰ፤
8. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን ዕገዳ በመተላለፍ ሥራውን ሲያከናውን ከተገኘ፤
9. ድርጅቱ ስለ ብቃት ማረጋገጫ ዕገዳ በአንቀፅ 31 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች በመተላለፍ ተመሳሳይ ጥፋቶችን በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ፈፅሞ ከተገኘ፡፡

## 31. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ስለመመለስ

1. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓይነት እና የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ ነባሩን የሥራ ፈቃድ ለባለሥልጣኑ መመለስ አለበት፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰረዘ፣ከታገደ፣በተቀመጠው የዕድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ የንግድ ስራውን ካቋረጠ ድርጅቱ ነባሩን ፈቃድ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ መመለስ አለበት፡፡

## 32. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ

ዕቃዎች ንግድ ድርጅት የተጣለበት ዕገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለዕገዳ ያበቃውን ጥፋት ካረመ ወይም ካስተካከለ ዕገዳው ሊነሳለት ይችላል፤

2. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የተሰረዘ ፈቃድ ሊተካለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝና ድርጅቱ ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ በማረምና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ የተደረገው የተሟላ ማስተካከያ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በተሰረዘው የምስክር ወረቀት ፋንታ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፤

## 33. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶችን ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ

ማንኛውም ሥራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ፣ዕገዳ ወይም ስረዛ የተጣለበት ድርጅት በእጁ ጥቅም ላይ መዋል የሚችል መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላላቸው ሌሎች ድርጅቶች ከተሟላ መረጃዎች ጋር የባለሥልጣኑ የምዝገባና ፈቃድ ባለሙያዎች በተገኙበት ማስተላለፍ ይገባዋል፡፡

## 34. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ስለመያዝ

1. ባለስልጣኑመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ጥራትና ደህንነት ላይ ጉድለት መኖሩን ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም በእንስሳትና በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካመነበት የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ጥራትና ደህንነት እስኪረጋገጥ ድረስ ምርቱ ተይዞና ለብቻው ተገልሎ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀፅንዑስ አንቀፅ1 መሠረት ተገልሎ እንዲቆይ የተደረገ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አስፈላጊው ፍተሻ ተደርጎ በጥቅም ላይ የማይውል መሆኑ ከተረጋገጠ  በኋላ ምርቱ ሊወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር ሊመለስ ይችላል፤
3. በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በመተላለፍ የሚደረግ የመኖ ሕገ-ወጥ ንግድና ዝውውር በተመለከተ ከኅብረተሰቡ ጥቆማ ሲደርሰው ባለሥልጣኑ ወይም ቅርንጫፍ መ/ቤቶቹ የምርቱን ጤናማነትና ደህንነት እንዲሁም ሕጋዊ አሠራሮችን ስለመከተላቸው ለማረጋገጥ ምርቱን መያዝ ይችላል፡፡

## 35. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ከገበያ ስለመሰብሰብ(Feed Products Recall)

1. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ያሰራጨው ምርት ጥራትና ደህንነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ጠቋሚ መረጃዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ማንኛውም ዓይነት ሽያጭ እንዳይደረግ የማስቆምና ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣
2. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ያስመጣው ወይም ያሰራጨው የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ጥራትና ደህንነት ጉድለት ካለውና ለእንስሳትና ለህብረተሰቡ ጤና ጎጂ መሆኑ ሲረጋገጥ በራሱ አሠራርና ወጪ ከገበያ የመሰብሰብ ግዴታ አለበት፣
3. በደህንነትና የጥራት ጉድለት ምክንያት ከገበያ የተሰበሰበዉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በላቦራቶሪ ፍተሻ ሲረጋገጥ በአንቀጽ 36 መሠረት እንዲወገድ መደረግ አለበት፣
4. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ብልሽት ምክንያቱ ተጣርቶ ችግሩ እንዲከሰት ያደረገው ድርጅት አግባብ ባላቸው ሕጎች አስተዳዳራዊ ወይም ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

## 36. ጥቅም ላይ የማይውሉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶችን ስለማስወገድ

1. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶችን ለይቶ የመያዝና ዝርዝራቸውን ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽንዑስ አንቀጽ1 መሠረት ጥቅም ላይ የማይውሉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶች በባለሥልጣኑ ውሳኔና የአሠራር መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ መደረግ አለበት፣
3. ማንኛዉም ጥቅም ላይ የማይውል መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃዎች የሚወገዱት አካባቢን በማይበክል ሁኔታ ለዚህ ተግባር በባለሥልጣኑ በወጣዉ የአወጋገድ መመሪያ መሠረት የሚከናወን ይሆናል፣

## 37. በባለስልጣኑ በሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት

1. በባለሥልጣኑ በሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ የሚቀርበው በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሠረት ይሆናል፣
2. ማንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ዕድሳት፣ዕገዳና ስረዛ ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ በሚወስዳቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ የተሰማው አካል አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በባለስልጣኑ ለተቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፣

3. የባለሥልጣኑ ቅሬታ ሰሚ አካልም የቀረበለትን ቅሬታ በማጣራት በ30 ቀናት ውስጥ አግባብነት ያለው ምላሽ ለአመልካቹ መስጠት ይኖርበታል፣
4. ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ባያገኝ ወይም የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ ሳያገኘው ቢቀር ቅሬታውን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## መረጃ የመያዝ ግዴታ፣ የንግድ ማስታወቂያና የአገልግሎት ክፍያ

## 38. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መረጃ ስለ መያዝ

1. ማ
ንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ስለሚያመርታቸው፣ ስለሚያስመጣቸውና ስለሚያከፋፍላቸው መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ዓይነቶች ምንጭና መነሻ ዝርዝር መረጃ (for traceability) ለይቶ መያዝ አለበት፣
2. ማንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ስለ አመረተው ወይም ስለአስመጣው፣ስለአከፋፈለው፣ስለላከዉ፣ስለተበላሸው፣የመጠቀሚያ ጊዜዉ ስላለፈበት እና ሌሎች ከመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፣
3. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ዝርዝር ደረሰኞች፣የክምችት መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርዶችንና ቢን ካርዶችን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፣
4. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቶችን የገዛበትና የሸጠላቸውን ድርጅቶች ስምና ሙሉ አድራሻ በዝርዝር መያዝ አለበት፣
5. ማ
ንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወቅታዊነት ቢያንስ ለ3 ዓመታት በአግባቡ የመያዝና ለባለሥልጣኑና ሌሎች ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም ጭምር ግልፅ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## 39. መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ማስታወቂያ አሠራር

ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ማስታወቂያ ሂደትና ይዘት የሚከተሉትን ዋና ዋና መሠረት ሐሳቦችን የተከተለ መሆን ይገባዋል፡-

1. ማ

ንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ማስታወቂያ አቅራቢ ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ማስታወቂያ ማውጣትና ማስነገር የለበትም፣

2. መ

ኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የንግድ ማስታወቂያ የመንግሥትን የማስታወቂያ ሥርዓትና ሥነ-ምግባር አክብሮ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፣

3. ለ

ማስታወቂያ የተዘጋጀዉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርት ለየትኛው የእንስሳት ዓይነት፣የዕድሜ ክልልና የምርት ክፍሎች መጠቀም እንደሚገባ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡ ለምሳሌ፡-ለታላቢ የዳልጋ ከብት፣ለጥጃ፣ለዳልጋ ከብት ማድለቢያ፣ለአጥቢ እናቲት በግ ወይም ፍየል፣ለበግ ወይም ፍየልማድለቢያ፣ለሥጋ ዶሮ፣ለዕንቁላል ጣይ ዶሮ፣ ለጫጩት፣ለአሳማ፣ ወ.ዘ.ተ በሚል ሁኔታ በግልጽ ተዘርዝሮ መገለጽ አለበት፤

4. መ

ኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ማስታወቂያ ከመውጣቱና አየር ላይ ከመዋሉ በፊት የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ምርቱ ከምን ዓይነት ግብዓቶች እንደተቀነባበረ፣የቅንብር ሂደትና የንጥረ ነገሮችን ዝርዝር መግለጫ የያዘ የማስታወቂያው ረቂቅ ጽሑፍ በማስታወቂያው አቅራቢ ድርጅት በኩል ለባለስልጣኑ ቀርቦ መፈቀድ አለበት፣

5. ማ

ስታወቂያው የሌላውን መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣አስመጪ፣አከፋፋይ ወይም የሌላውን ተወዳዳሪ ድርጅት ምርት፣ጥራት ደረጃ እና ደህንነት እንዲሁም የንግድ ምልክት ማጥላላት፣አሳንሶ ማቅረብ ከማስታወቂያ ሥነ-ምግባር ውጭ እንዳይሆን ባለሥልጣኑ ለዚህ ጉዳይ በሚመድበው ክፍልና ባለሙያ አማካኝነት ታይቶ መፈቀድና ማለፍ ይገባዋል፣

6. በ

ምርት ገላጭ ጽሁፍ ላይ ከተመለከተው የእንስሳት ዓይነት፣የዕድሜና የምርት ክፍል ውጪ መመገብ የተከለከለ ስለመሆኑ መጠቀስና መገለጽ አለበት፣

7. ማ

ስታወቂያው ሲወጣም ሆነ ሲነገር ከሌላ የእንስሳት መኖ፣የእንስሳት መድኃኒት፣ለሰው ምግብ ሊውሉ ከሚችሉ ማስታወቂያዎች ጋር የሚጣረስ መሆን የለበትም፣

8. በ

መኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ማስታወቂያ ላይ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ

አጠቃቀምን በተመለከተ በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በባለሙያ መታገዝ እንዳለበት አበክሮ መገለጽ አለበት፣

9. በ ማስታወቂያው ላይ ለእንስሳት የሚቀርብ መኖ ወይም መኖ ጥሬ ዕቃ ንጽህናው በተጠበቀ ዕቃና ለእንስሳት ክብካቤ ኃላፊነት በተሰጠው ሰው እንዲሁም በእንስሳት አመጋገብ ባህሪ ላይ ተመርኩዞ መሰጠት እንዳለበት መገለጽ ይገባዋል፣

10. የ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ማስታወቂያ የእንስሳት ጤንነትንና ደህንነት መርሆዎችን በማያዛባና በማይጎዳ መልኩ መዘጋጀትና መውጣት አለበት፣

11. የ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ማስታወቂያ የሀገሪቱን ህዝብ ባህል፣እምነትና ተለምዶ በማይጻረር መልኩ በጥንቃቄ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፣

12. በማስታወቂያ የሚነገረው መኖ ወይም መኖ ጥሬ ዕቃ የእንስሳት በሽታን ያድናል ወይም ይፈውሳል፣ጤና ያሻሽላል ተብሎ መነገር የለበትም፣

13. እንደ መኖው ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ዓይነት የእንስሳት ምርታማነትን የሚደግፍ፣ የሚረዳ፣ጉልበት የሚሰጥ ለእንስሳት አካላት ዕድገት ጠቃሚ ነው ተብሎ ሊነገር ይችላል፤

14. በ ቀጥታ ለእንስሳት የማይሰጥ የመኖ ተጨማሪ ንጥር ነገር ከምግብና ከውሃ ጋር በማመጣጠን የሚሰጥ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ በባለሙያና በፋብሪካው ገላጭ ጽሑፍ በሚያዘው መሠረት ብቻ እንደሚሰጥና ጠቃሚነቱም መኖን ለማዋሃድ፣ለመፍጨት እንዲሁም የተሻለ ምርት ለመስጠት የሚያግዝ እንዲሁም ለተጠቃሚው የጎንዮሽ ጉዳት የማያስከትል ስለመሆኑ በመግለጽ መውጣት ይችላል፤

15. በኤሌክትሮኒክስ ግብይት (e-marketing) የሚካሄድ ግንኙነት የድርጅቱን የንግድ ስም፣ ሙሉ አድራሻ፣የምርት መለያ ቁጥር (butch number)፣ለየትኛው የእንስሳት ምርትና ዕድሜ ክፍል መዋል እንዳለበት፣ምርቱ የታሸገበት ቀን፣የተመረተበት ቀንና ዓ.ም፣ በመጋዘን የሚቆይበት ጊዜ ወይም መጠቀሚያ ጊዜ (storage life)፣ የተመረተበት ሀገር በዝርዝር መጠቀስ አለበት።

## 40. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ

1. ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
2. ባለሥልጣኑ በማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት ያገኛቸው የአሠራር ግድፈቶች፣የተረጋገጠ ተጨባጭ ጥቆማዎችና መረጃው ለሕብረተሰቡ ባለመነገሩ በእንስሳትና በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ሲታመን መረጃዎቹን አመቺ ሆኖ ባገኘው የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
3. ማንኛውምየመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ስምና አድራሻ የሚገልፅ፣ሊነበብ በሚችል ጉልህ ፊደል ቢያንስ ድርጅቱ በሚገኝበት የአካባቢ ቋንቋ ወይም በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ፅፎ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ ላይ የድርጅቱን ማንነት ሊያመላክት በሚችል መልኩ ማኖር አለበት፣
4. ባለሥልጣኑ ማንኛውም ጠቃሚ የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ባለሙያዎች ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
5. በባለሥልጣኑ ምስጢር ተብለው ከተያዙ መረጃዎች በስተቀር ስለ ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት ይችላል።

## 41. የአግልግሎት ክፍያ

ማንኛዉም መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅት በባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ባለው አካል በሚወስነው የክፍያ ተመን መሠረት ክፍያዉን በቅድሚያ መፈጸም ይኖርበታል። የአገልግሎት ክፍያው መጠን ዝርዝር ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይሆናል።

# ክፍል ስምንት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 42. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ሀ. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ሰርኩላር፣ደብዳቤ፣የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፤

ለ. ቀደም ሲል ሥራ ላይ ዉሎ የነበረዉ “የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣ አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይ፣ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ መስጫ አሠራር መመሪያ ቁጥር 03” በዚህ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል።

## 43. መመሪያውን ስለማሻሻል

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ይህን መመሪያ እንደገና ማሻሻል ይችላል፡፡

## 44. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ.......................ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ጠርዙ ዳያ ደጋጋ (ዶ/ር)**

**የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**

## 45. ዕዝሎች

**የእንስሳትመድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን**
**Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority**

ዕዝል 01

### የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ቅጽ

1. የአመልካቹ ሙሉ ስም ____________________________________________
2. የአመልካች ድርጅት ስም ________________________ የንግድ ስም___________________________
3. አመልካቹ በድርጅቱ ውስጥ ያለው ኃላፊነት______________________________________________
4. የድርጅቱ ባለቤትሙሉስም___________________________________________________________

   አድራሻ ፡- ክልል _________________ ክ/ከተማ (ዞን) ወረዳ _________

   ከተማ_______________________

   ስልክ ቁ.__________ ሞባይል ________________
   ኢ.ሜይል_________________________________________

5. የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ ድርጅቱ አድራሻ

   ክልል___________________ (ዞን)
   ክ/ከተማ__________ወረዳ_________________ከተማ_________________
   ስልክ ቁ______________ሞባይል_____________________ኢ.ሜል___________________________
   የቦታው ልዩ መጠሪያ____________________________________________________________
6. የድርጅቱ ዓይነት

   የመኖ አምራች ☐ መኖ አስመጪ ☐ የመኖ አከፋፋይ ☐ መኖ ላኪ ☐ የመኖ ችርቻሮ ☐

   የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ☐ የመኖ ጥሬ ዕቃአስመጪ ☐ የመኖ ጥሬ ዕቃአከፋፋይ ☐ የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ☐

7. የድርጅቱ የመኖ ቴክኒክ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ
   7.1 ሙሉ ስም ____________________________
   7.2የትምህርትደረጃ _______________________
   7.3 የባለሙያው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቅጅ (አብሮ ይያያዝ)
   7.4 የሠራተኛው/ባለሙያውየውልስምምነትናየትምህርትማስረጃ ቅጅ (አብሮ ይያያዝ)

8. እኔ ______________________ የተባልኩኝየመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣ አስመጪ ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የምዝገባና የሥራ ፈቃድ መስጫ መመሪያላይየተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላሁ ስለሆነ ድርጅቱ ታይቶየብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትእንዲሰጠኝእጠይቃለሁ፡፡

   ፊርማ ___________________________

   ቀን ________________________

9. <u>ለቢሮሥራብቻየሚያገለግል</u>

   ማመልከቻውን የተቀበለው ባለሙያ ስም ______________________________
   ማመለልከቻውን የተቀበለበት ቀን ___________________
   መልስ የሚሰጥበት ቀን (ቀጠሮ) ______________________

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

ዕዝል 02

## የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች መገምገሚያ ቅፅ

ድርጅቱ ስም ____________________ የምርት ዓይነት ____________________

ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል __________ ዞን/ክፍለ ከተማ ______________ወረዳ ________

ከተማ____________

ቀበሌ ____________ የቦታው ልዩ መጠሪያ ____________ ስልክ ቁጥር ________ ሞባይል ______________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ____________________________

| ተ ቁ | የመገምገሚያመስፈርት | የመመዘ ኛነጥብ | የተሰጠነ ጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ድርጅቱየተቋቋመበትቦታለመኖወይም ለመኖ ጥሬ ዕቃ ብክለትያለውተጋላጭነት | 8 | |
| 2 | የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማመረቻዉ በአካባቢዉ ህብረተሰብ ላይ የሚያስከትለዉ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖር | 7 | |
| 3 | የመኖ አመራረትን በኃላፊነት የሚመራ ባለሙያ ስለመቀጠሩ የተረጋገጠ ማስረጃ ስለመኖሩ | 6 | |
| 4 | የመኖ ጥራትና ደህንነት የዉስጥ ተቆጣጣሪ ባለሙያ ስለመቀጠሩ የተረጋገጠ ማስረጃ ስለመኖሩ | 6 | |
| 5 | ለፍሳሽናደረቅቆሻሻአያያዝ፣አወጋገድ ሥርዓት የተመቻቸሁኔታያለውአስፈላጊግንባታናቁሳቁስ ስለመኖሩ | 6 | |
| 6 | የጥሬ ዕቃ ቅበላ አሠራርር መመሪያ (SOP) በድርጅቱ ስለመዘጋጀቱ የተረጋገጠ ማስረጃ ስለመኖሩ | 8 | |
| 7 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መጠንን ያገናዘበ መጋዘን ስለመኖሩ፣ከፍታና የአየር ዝዉዉር ተስማሚነት | 5 | |
| 8 | በመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መጋዘን ዉስጥ የሙቀትና እርጥበት መለኪያ መሣሪያ ስለመኖሩና ስለመረጋገጡ | 5 | |
| 9 | በመኖ አመራረት ሂደት ዉስጥ የተለዩ የአደጋ መንስኤ ክፍሎች ተመዝግበዉ ስለመያዛቸዉ ማስረጃ ስለመኖሩ | 6 | |
| 10 | በማመረቻና ማከማቻክፍሎች ውስጥያለውየብርሃንናየአየርዝውውርሁኔታበቂስለመሆኑ | 5 | |
| 11 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ክምችት በቁመደርደሪያ/ፓሌትስለመኖሩናየማቴሪያሉዓይነት | 5 | |
| 12 | ለተበላሹ፣የመጠቀሚያጊዜያለፈባቸውመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማቆያየተለየማከማቻ ክፍል መኖሩ | 5 | |
| 13 | የማምረቻ፣ማከማቻመጋዘንበሮች፣መስኮቶች፣የአየርማስገቢያ ሁኔታ፣ነፍሳትንናተባይንእንዲሁምመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውንሊበክሉከሚችሉነገሮችየመከላከልአመችነት | 5 | |
| 14 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃመጠን መለኪያ ሚዛንስለመኖሩና ትክክለኛነቱ ስለመረጋገጡ | 5 | |
| 15 | የድንገተኛአሳትአደጋማጥፊያመሳሪያስለመኖሩ | 5 | |
| 16 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃመሸጫናስርጭትመረጃአያያዝ ስርዓትስለመኖሩ | 5 | |
| 17 | የሠራተኞችየሥራጤናማነትናደህንነትመጠበቂያክፍሎችናየመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ማቴሪያሎች ስለመኖሩ | 4 | |
| 18 | መፀዳጃናየእጅመታጠቢያክፍልመኖሩ | 4 | |
| | ጠቅላላድምር | 100 | |

**ማሳሰቢያ:**

በሰንጠረዡላይበተቀመጠው መስፈርት መሰረት 70% እና በላይ ያገኘ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትለማግኘትብቁ ያደርገዋል፡፡

የባለሙያዎች ማጠቃለያ አስተያየት ______________________________________________

______________________________________________________________

የባለሙያዎች ስም ፊርማ

1.____________________ ______ ቀን

2.____________________ _______ ________________

3.____________________ ______

የኃላፊው አስተያየት ________________________________________

ስም ____________________ ፊርማ ____________________ቀን ______________

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

**ዕዝል 03**

### የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላና ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች መገምገሚያ ቅፅ

ድርጅቱ ስም ______________________________________________ የምርት ዓይነት ____________________________
ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል ____________ ዞን/ክፍለ ከተማ __________________ወረዳ __________
ከተማ______________
ቀበሌ ______________ የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________ ስልክ ቁጥር _________ ሞባይል _________________
የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ __________________________________

| ተቁ | የመገምገሚያመስፈርት | የመመዘኛ ነጥብ | የተሰጠነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ድርጅቱንበቴክኒክኃላፊነትየሚመራየመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ሽያጭሠራተኛ /ባለሙያየትምህርትዝግጅትሁኔታ | 10 | |
| 2 | የማከማቻ መጋዘኑ የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃንሊበክሉከሚችሉነገሮችየጸዳና የመከላከልሁኔታ | 10 | |
| 3 | የመጋዘንከፍታና ስፋት ከሚከማቸውመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ መጠንናየአየርሁኔታጋርየሚኖረውተስማሚነት | 8 | |
| 4 | የሙቀትእናየእርጥበትመለኪያመሣሪያበመጋዘኑስለመኖሩና ስለመረጋገጡ | 8 | |
| 5 | ለፍሳሽናደረቅቆሻሻአያያዝሁኔታያለውአስፈላጊግንባታናቁሳቁስ ስለመኖሩ | 8 | |
| 6 | ጥቅም ላይ የማይዉሉ መኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማቆያየተለየየክምችት ክፍል ስለመኖሩ | 7 | |
| 7 | የማከማቻክፍሉጣሪያየተሰራበትማቴሪያልሙቀትናከቀጥተኛየፀሀይብርሃንየመከላከልሁኔታዉ | 7 | |
| 8 | የማከማቻመጋዘኑበር፣መስኮትእናየአየርማስገቢያዉ፣ነፍሳትንናተባይንየመከላከል ሁኔታ | 7 | |
| 9 | በማከማቻመጋዘኑውስጥያለውየብርሃንናየአየርዝውውርሁኔታበቂስለመሆኑ | 6 | |
| 10 | መኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃውንለማቆየትየሚያስችልበቂመደርደሪያ/ፓሌትመኖሩንናየማቴሪያሉዓይነት | 7 | |
| 11 | የድንገተኛእሳትአደጋማጥፊያመሳሪያስለመኖሩ | 6 | |
| 12 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃመሸጫናስርጭትመረጃመያዣስርዓትስለመኖሩ | 6 | |
| 13 | የመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃመመዘኛሚዛንበመጋዘኑስለመኖሩና ስለመረጋገጡ | 5 | |
| 14 | መፀዳጃናየእጅመታጠቢያክፍልስለመኖሩ | 5 | |
| | ጠቅላላድምር | 100 | |

**ማሳሰቢያ፡**

በሰንጠረዡላይበተቀመጠው መስፈርት መሰረት 70% እና በላይ ያገኘ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትለማግኘትብቁ ያደርገዋል፡፡
የባለሙያዎች ማጠቃለያ አስተያየት ____________________________________________________________

____________________________________________________________________________

የባለሙያዎች ስም ፊርማ

1.______________________ ______ ቀን
2.______________________ _______ __________________
3.______________________ ______

የኃላፊው አስተያየት _______________________________________________________
ስም ____________________ ፊርማ ____________________ቀን _______________

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

**ዕዝል 04**

**የፈሳሽ መኖ ወይም ፈሻሽ የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላና ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች መገምገሚያ ቅፅ**

ድርጅቱ ስም ____________________________________________ የምርት ዓይነት ___________________________

ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል ___________ ዞን/ክፍለ ከተማ ________________ወረዳ _________

ከተማ_____________

ቀበሌ ______________ የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________ ስልክ ቁጥር _________ ሞባይል _________________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ________________________________

| ተቁ | የመገምገሚያመስፈርት | የመመዘኛ ነጥብ | የተሰጠነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ድርጅቱንበቴክኒክኃላፊነትየሚመራየመኖወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ሽያጭሠራተኛ/ባለሙያየቅጥርና ትምህርትዝግጅትሁኔታ | 12 | |
| 2 | የ ፈሳሽ መኖ ወይም የፈሳሽ መኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ ዲፖ'/ሮቶ በአግባቡ ስለመገንባቱ ወይም ስለመተከሉ | 12 | |
| 3 | የ ፈሳሽ መኖ ወይም የፈሳሽ መኖ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ ዲፖ'/ሮቶ ጥሬ ዕቃዉንሊበክሉከሚችሉነገሮችየጸዳ አካባቢ ላይ ስለ መገናባቱና የመከላከልሁኔታ | 10 | |
| 4 | የፈሳሽ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ማመላለሻ ቦቴ ወይም ተስማሚ መያዣ ሮቶ ስለመኖሩ | 8 | |
| 5 | የዲፖ'ዉ ወይም ሮቶዉ መጠን ከሚከማቸውጥሬ ዕቃ መጠንናየአየርሁኔታጋርየሚኖረውተስማሚነት | 8 | |
| 6 | ፍሳሽናደረቅቆሻሻወደ ዲፖ'ዉ ወይም ሮቶዉ እንዳይገባ የመከላከል ሁኔታአስፈላጊግንባታናቁሳቁስ ስለመኖሩ | 8 | |
| 7 | የማከማቻዲፖ'ዉ ወይም ሮቶዉ የሙቀትናከቀጥተኛየፀሀይብርሃንየመከላከልሁኔታዉ | 8 | |
| 8 | የማከማቻዲፖ'ዉ ወይም ሮቶዉ ለመቅዳትና ለማከፋፈል የአሠራር አመቺነትና የብክለት መከላከል ሁኔታ | 7 | |
| 9 | የፈሻሽ ጥሬ ዕቃመመዘኛሚዛንበመጋዘኑስለመኖሩና ስለመረጋገጡ | 7 | |
| 10 | የድንገተኛአሳትአደጋማጥፊያመሳሪያስለመኖሩ | 7 | |
| 11 | የፈሳሽ ጥሬ ዕቃመሸጫናስርጭትመረጃመያዣስርዓትስለመኖሩ | 7 | |
| 12 | መፀዳጃናየእጅመታጠቢያክፍልስለመኖሩ | 6 | |
| | ጠቅላላድምር | 100 | |

**ማሳሰቢያ:**

በሰንጠረዡላይበተቀመጠው መስፈርት መሰረት 70% እና በላይ ያገኘ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትለማግኘትብቁ ያደርገዋል፡፡

የባለሙያዎች ማጠቃለያ አስተያየት ______________________________________________________________

______________________________________________________________________________

የባለሙያዎች ስም ፊርማ

1.______________________ ______ ቀን

2.______________________ _______ __________________

3.______________________ ______

የኃላፊው አስተያየት _________________________________________________________

ስም ____________________ ፊርማ ____________________ቀን _______________

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል 05**

## በተስማሚነት ፍተሻ ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማሟላት ከድርጅቱ ጋር የሚገባ መተማመኛ ሰነድ

የድርጅቱስም ________________________________የምርትዓይነት ____________________________

የድርጅቱአድራሻክልል ______________ ዞን/ክ/ከተማ ________________ወረዳ ___________

ከተማ ______________

ስልክ _______________ ሞባይል _________________E-mail: ____________________

የድርጅቱባለቤት/ተወካይ ____________________________________________

| ተ.ቁ | በድርጅቱውስጥየተገኙክፍተቶች | በድርጅቱመወሰድያለባቸውየማስተካከያእርምጃዎች | የጊዜወሰን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |

| | |
|---|---|
| የፈታሽባለሙያዎችስምፊርማ | |
| 1. | የድርጅቱባለቤት/ተወካይ |
| 2. | ስም |
| 3. | ፊርማ |
| ቀን | ቀን |
| | |

የእንስሳትመድኃኒትናመኖአስተዳደርናቁጥጥርባለልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

ቁጥር ________________

ቀን __________________

**ዕዝል 06**

**የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይ፣ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ደርጅት የብቃት ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት**

Certificate of Competence for Feed or Feed Imput Processors, Importers, Exporters, Wholesalers,Retailers Organizations

የድርጅቱ ስም ____________________ የንግድ ስራ ዓይነት______________________________

Name of business organization Buisness type

የሚይዘው የምርት ዓይነት________________________________________________________________

Product Type

የድርጅቱ አድራሻ

Address of the organization

ክልል__________________ዞን/ክ/ከተማ ________________ወረዳ ___________ከተማ _____________

Region Sub city/Zone Woreda City

ቀበሌ______________ የቤ/ቁጥር___________ስ/ቁጥር ___________________ፋክስ_______________

Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም _____________________________________

Owners Full Name

ባለስልጣኑ ያወጣቸውን መስፈርቶች፤ ድርጅቱ ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አሰተዳደርናቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥተር 728/2004 አንቀጽ 19 መሠረት ለ________________________________ የሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ ቁጥር __________________ ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued for Business type _______________________________licencing category _____________________, upon fulfillment of compliances set by the Authority in accordance with Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority, Proclamation No. 728/2011 Article 19.

___________________________ ______________________

የኃላፊ ፊርማ የተሰጠበት ቀን

Signature of Authorized Person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሷል 201____________ | ታድሷል 201_______ | ታድሷል 201_______ |
| Renewed 201_________ | Renewed 201_____ | Renewed 201 _______ |
| የደረሰኝ ቁጥር __________ | የደረሰኝ ቁጥር _______ | የደረሰኝ ቁጥር ________ |
| Rec/no_________________ | Rec/no ______________ | Rec/no _____________ |
| ፊርማ ______________ | ፊርማ _____________ | ፊርማ ___________ |
| Sig ________________ | Sig ______________ | Sig _____________ |

የእንስሳት መድኃኒትና መኖአስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል** 07

**የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ናሙና መውሰጃ ማሳወቂያ ቅጽ**

እኛ ስማችን ከታች የተገለፀው የባለስልጣኑ ባለሙያዎችና ኢንስፔክተሮች የሆንን በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ (ሐ) ና (መ) መሠረት የሚከተለውን የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ናሙና ለምርመራ ዓላማ ከድርጅቱ የወሰድን መሆናችንን እናረጋግጣለን፡፡

1. የናሙናው ባለቤት ድርጅት ስም ______________________________
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር______________________________
3. አድራሻ______________________________
4. የናሙናው መጠሪያ ስም እና ዓይነት______________________________
5. መጠን______________________________
6. የምርት መለያ ቁጥር (batch No.) ______________________________
7. የተመረተበት ቀን ______________________________
8. የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን______________________________
9. የአምራቹ ድርጅት ስም______________________________
10. ናሙናው የተወሰደበት ቦታ______________________________
11. ናሙናው የተወሰደበት ምክንያት______________________________

ናሙናውን የወሰዱ ባለሙያዎች ወይም ኢንስፔክተሮች ሙሉ ስምየድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ

1. ____________________ፊርማ ______________ ስም ____________
2. ____________________ፊርማ ______________ ፊርማ __________
3. ____________________ፊርማ ______________ ቀን __________

ናሙናው የተወሰደበት ቀን ________________ ሰዓት ________________

የባለሙያዎች ወይምኢንስፔክተሮች ኃላፊ አስተያየት

______________________________________________________________

______________________________________________________________

የኃላፊው ሙሉ ስም______________________________

ፊርማ ______________________________

ቀን ______________________________